አላ ፡ እግንቱ ፡ መልእክታት ፡ ዘአረጋዊ ፡ መንፈላዊ ፡ ዘኮነ ፡ ይፈ
ንም ፡ ጎበ ፡ ስለ ፡ አሐዱ ፡ እምፍቁራኒሁ ።

ድርሳኑን ፡ ጨርሶ ፡ መልእክቱን ፡ አመጣ ። ዮሐንስ ፡ ያየዉን ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጽፎ ፡ ይሰድለታል ። አረጋዊም ፡ የዚህን ፡ ምላሽ ፡ እ
የ ፡ ጻፈ ፡ ይሰድለታል ። አንድም ፡ አረጋዊ ፡ ይህን ፡
ይህን ፡ አድርግ ፤ ይህን ፡ ይህን ፡ አታድርግ ፡ ብሎ ፡
ጽፎ ፡ ይሰድለታል ። የሚሰደዉም ፡ ለሱ ፡ ብቻ ፡ አ
ይደለም ፤ ለበቁት ፡ ሁሉ ፡ እየ ፡ ጻፈ ፡ ይሰድላቸዋል ።
እነዚያ ፡ እየ ፡ ተመለከቱ ፡ ይተዉታል ። እሱ ፡ ሣን ፡
ሰብስቦ ፡ ድርሳኑን ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፤ መልእክቱን ፡
አርባ ፡ ስምንት ፡ አድርጎ ፡ ጽፎታል ። አሁን ፡ ድርሳ
ኑን ፡ ጨርሶ ፡ መልእክቱን ፡ አመጣ ። ከወዳጆቹ ፡ ላ
ንዱም ፡ ላንዱም ፡ ጽፎ ፡ ይልክላቸው ፡ የነበረ ፡ የአ
ረጋዊ ፡ መልእክታት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

መልእክት ፡ ቀዳሚት ።

ጎበ ፡ አሐዱ ፡ አረጋዊ ፡ ቅዱስ ፡ ወፍጹም ፡ ዘይፈኢ ፡ ጎቡኣተ ።

ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ ለሚያይ ፤ ክቡር ፡ ፍጹም ፡ ወደ
ሚሆን ፡ ወዳንዱ ፡ አረጋዊ ፡ የተላከች ፡ መዠመሪያ
ዪቱ ፡ ከታብ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ይቤ ፤ እልእክ ፡ ጎቤክ ፡ እ ፡ ዘበብርሃን ፡ አምላክዊ ፡ ዘሥዉጥ ፡ ውስ
ተ ፡ ንፍሱ ፡ የኀሥሥ ፡ ጎቡኣተ ።

በልቡናህ ፡ በደረ ፤ አምላክ ፡ በሚገልጸው ፡ ዕውቀ
ት ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢርን ፡ ወደምትመረምር ፡ ወዳን
ተ ፡ ጽፌ ፡ እልካለኁ ።

ወምሥጢራተ ፡ መንፈስ ፡ ዘበመንፈስ ፡ ይትጌህር ።

የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ምሥጢር ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ለምትማር ፡ ላንተ ።

ወክክብ ፡ ብዙኃ ፡ ጸዳል ፡ ዘውስተ ፡ ልቡ ፡ ይበርህ ።

ብርሃኑ ፡ ፍጹም ፡ የሚሆን ፡ ክርስቶስ ፡ በልብህ ፡ አ
ድሮ ፡ ለሚያበራ ፡ ላንተ ።

ወበብርሃን ፡ ዘኀሩር ፡ ውስቴቱ ፡ ይትወሐድ ፡ ምስለ ፡ ብርሃን ።

በተሰጠህ ፡ ዕውቀት ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ለምትዋሐድ ።

ወአጽናፈ ፡ ዓለም ፡ ተመልአ ፡ እምጸጋሁ ።

በራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ላንተ ፡ ከተሰ
ጠው ፡ ጸጋ ፡ የተመላ ።

ወእምኀበረ ፡ መንፈስ ፡ ዘኀሩር ፡ ላዕሌሁ ።

በንተ ፡ አድሮ ፡ ከለ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምሥጢር ፡
የተመላ ፤ ላንተ ፡ አልክልኻለኁ ።

እ ፡ ዘያዜኑ ፡ ነፋሰ ፡ ሕይወት ፡ እምኀበ ፡ ሕይወት ።

ከእግዚአብሔር ፡ የሕይወት ፡ መዓዛን ፡ የምታሸት ፡
ሆይ ።

ወይክውን ፡ ላዕሌሁ ፡ ዕውበ ፡ ጲኣተ ፡ ሞት ፡ በአእምሮቱ ።

እንዲጐዳ ፡ በማወቅህ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ኀጢአት ፡ ጭ
ንቅ ፡ የሚሆንብህ ።

አ ፡ እግዚአየ ፡ አበ ፡ ቅዱሳን ፤ ነኖ ፡ ሊተ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡
እጸንሕ ፡ ተራክቦተክ ።

የቅዱሳን ፡ አባት ፡ የምትሆን ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ ካንተ ፡
ጋራ ፡ ለመገናኘት ፡ ደጅ ፡ ስጠና ፡ እነሆ ፡ ብዙ ፡ ዘ
መን ፡ ነው ።

ዘውእቱ ፡ ርእየ ፡ ገጽከ ፡ ዘምሉእ ፡ ቅድስና ፤ ወኮዛዜ ፡ በእግዚአብሔ
ር ።

ይኸውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቅድስናን ፤ ክብርን ፡ የ
ተመላ ፡ ፊትህን ፡ ማየት ፡ ነው ።

ወእስከ ፡ ይእዜ ፡ አእጋርየ ፡ አስተዳጎራኢ ፡ እምን ፡ ዝንቱ ።

እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ወዳንተ ፡ ከመምጣት ፡ እግሮ
ቼ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አሉብኝ ።

ወላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ምክንያት ፡ መንፈስ ፡ ስምዐ ፡ ይኩንክ ።

አስተዳጎራኢ ፡ ያልሁት ፡ ነገር ፡ ሐሰት ፡ ሁኖ ፡ እን
ደ ፡ ሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክር ፡ ይሁንህ ። አን
ድም ፡ በዚች ፡ ከታብ ፡ ያለ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሐሰት ፡ ሁ
ኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክር ፡ ይሁን
ህ ።

እግዚአብሔር ፡ ይጸግወኒ ፡ ንጽሮተ ፡ ገጽከ ።

እግዚአብሔር ፡ ፊትህን ፡ ለማየት ፡ ያብቃኝ ።

ወያስተፍሥሖ ፡ ለልብየ ፡ እምሐዘናቲሁ ።

ልቡናዬን ፡ ከሐዘኑ ፡ ለይቶ ፡ ደስ ፡ ያሰኘው ።

እምቅድመ ፡ ዕርበተ ፡ ፀሐይ ፡ ዘንግደትክ ፡ ጎበ ፡ ሀገረ ፡ ኵሎሙ ፡ ብ
ርሃናት ፤ ወኀሰመ ፡ ኀለግት ፡ ዘለኀለም ።

የመላእክት ፤ የጻድቃን ፡ ዓለም ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፤ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የምት
ሔድበት ፡ ፀሐይ ፡ ዕድሜህ ፡ ሳይገባ ፡ ፈትህን ፡ ለማ
የት ፡ ያብቃኝ ።

እመ ፡ ከመ ፡ በህየ ፡ ዕበ ፡ ይክድንክ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢ
ይትክህሰኒ ፡ ንጽሮተክ ።

በንጽሐ ፡ ልቡና ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ብርሃን ፡ የሸፈነህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምናልባ
ት ፡ አንተን ፡ ማየት ፡ አይቻለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

እስመ ፡ ኢይበውኡ ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡ ዘኢያመረ ፡ መከራሃ ፡ በዝየ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ መከራነቷን ፤ መከራዋን ፡ ያላወቀ ፡ ሰው ፡ ንጽሐ ፡ ልቡናን ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አያገኟምና ።

ይጼለላ ፡ አዕይንተ ፡ ልቡናሁ ፡ እምጸዳለ ፡ ብርሃናት ፡ ዘደመናት ፡ እስ ፡ ይወፅኡ ፡ እምህየ ።
ከጌታ ፡ የሚገኙ ፡ ምሉአን ፤ ስፋሓን ፡ የሚሆኑ ፡ ብርሃናትን ፡ ከማየት ፡ አዕይንተ ፡ ልቡናው ፡ ይሸፈናሉ ።

ወይክልኦሁ ።
ከማየት ፡ ይከለክሉታል ።

ወጎሊናስ ፡ ዘሠረቀ ፡ ውስቴቱ ፡ ጸዳለ ፡ ሕይወት ፡ ለአሠንዮቅ ፡ በዝየ ፡ ውእቱሰ ፡ ዕበ ፡ ይትፈለጥ ፡ እምሥጋሁ ፡ ይትካፈል ፡ ርስቶ ።
ደስ ፡ ሊያሰኘው ፡ ጸዳለ ፡ ሕይወት ፡ ጌታ ፡ ያደረበት ፡ ጎሊና ፡ ግን ፡ በሞት ፡ ከሥጋው ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ የጌታ ፡ ርስትነቱን ፤ ርስቱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሳል ።

ወየሐውር ።
በዚያው ፡ ይኖራል ።

ወይረክበ ፡ ለገዙ ፡ ብርሃን ፡ ፍትው ፡ ዘእምፀሐዩ ፡ ለብርሃን ፡ ጎስማት ፡ ዐቢይ ፡ ወልዑል ።
ዐቢይ ፡ ልዑል ፡ ከሚሆን ፤ የጻድቃን ፡ የመላእክት ፡ ብርሃን ፡ ከሚሆን ፡ ከአብ ፡ ከተገኙ ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሳይለይ ፡ ብርሃን ፡ አብን ፡ ያየዋል ።

አኮኬ ፡ ሥልጣን ፡ ይእዜ ፡ ለልሳን ፡ ዘይትከሠሎ ፡ ይንበብ ፡ ዝኆኔ ፡ ጎድረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በውስተ ፡ ጎሊናት ፡ ትዱሳት ።
በንጹሓት ፡ ጎሊናት ፡ እግዚአብሔር ፡ የማደሩን ፡ ነገር ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ሳንደበት ፡ አይቻለዉም ።

አላ ፡ ባሕቱ ፡ ትርጓሜሁሰ ፡ ለምሥጢር ፡ ዐቢይ ፡ ዘከመ ፡ የጎድር ፡ ውስተ ፡ ጎሊናት ፡ ጽሩያት ፡ ናሁ ፡ ተጎትመ ፡ ውስተ ፡ አርምሞ ።
በንጹሓት ፡ ጎሊናት ፡ እንዲያድር ፡ የዚህ ፡ ምሥጢር ፡ ነገሩ ፡ ባርምሞ ፡ ተወስኑዋል ፡ እንጂ ፤ አይቻለዉም ።

እስመ ፡ በብሔር ፡ ንኩር ፡ ያስተርኢ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፍቁራኒሁ ።
እግዚአብሔር ፡ ለወዳጆቹ ፡ በንጽሐ ፡ ልቡና ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይገለጻልና ።

ወይፈስሑ ፡ ይደመሙ ፡ እምኒ ።
መልኩን ፡ አይተው ፡ እንዲያደንቁ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ወበተደሞቱ ፡ ያረምም ፡ ውክቶሙ ፡ በርእየ ፡ ምሥጢራቲሁ ።
ምሥጢሩን ፡ አይቶ ፡ በመደመም ፡ ልቡናቸው ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

ወበጺሖሙ ፡ ሀገረ ፡ ዘንኩር ፡ ራእያ ።
ብርሃንዋ ፡ ልዩ ፡ ወደሚሆን ፡ ንጽሐ ፡ ልቡና ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ልቡናቸው ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

ሀገር ፡ እንተ ፡ ታደምቃ ።
ይህቺውም ፡ የምታስደንቅ ፡ ናት ።

ሐውርኒ ፡ ዘየዐውዳ ፡ አርምሞ ፡ ውእቱ ።
የሚከባትም ፡ ቅጽሯ ፡ አርምሞ ፡ ነው ።

ወእመ ፡ ፈቀደ ፡ ጎሊና ፡ ከመ ፡ ይትዋሃእ ፡ ወይክሥት ፡ ግብራ ፡ በአልዕሎ ፡ ቃል ፡ ይረክብዎ ፡ አድያማተ ፡ አርምሞ ።
ጎሊና ፡ ቃሉን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ግብሯን ፡ ገልጾ ፡ ሊናገር ፡ ቢወድ ፡ የአርምሞ ፡ ተራሮች ፡ ይከቡታል ።

ወያረምም ።
ያዩዋን ፤ የሰማዒን ፡ ምሥጢር ፡ ከመናገር ፡ ይከለክላል ።

ለፀገረ ፡ ጽግዌሰ ፡ ወህድአት ፡ ኢይትክፅታ ፡ ምሥጢራቲሃ ፡ ዘእንበለ ፡ በአርምሞ ።
በህድአት ፡ በጽማዌ ፡ የምትገኝ ፡ የንጽሐ ፡ ልቡና ፤ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ምሥጢር ፡ በአርምሞ ፡ ይወሰናል ፡ እንጂ ፡ አትነገርም ።

ወእመሰ ፡ አለ ፡ የጎድርዎ ፡ ለይእቲ ፡ ሀገር ፡ ይትጌህርዎ ፡ ለአርምሞ ፡ እምሥጢራቲሃ ።
ምሥጢሯን ፡ የለመዱ ፡ ፍጹማን ፡ ከርቀቷ ፡ የተነሣ ፡ አርምሞን ፡ የሚማሯት ፡ ከሆነ ።

ወእለሰኬ ፡ ኢኮኑ ፡ ልሙዳን ፡ በምሥጢራቲሃ ፡ አይኑ ፡ ተደሞ ፡ ወእንኩሮ ፡ ዘይረክቦሙ ፡ እምኮሱ ፡ ተወውኮ ፡ ዕበ ፡ ትትከሠት ፡ ሶሙ ።
ምሥጢሯን ፡ ያለመዱ ፡ ወጣንያንማ ፡ በተገለጸችላቸው ፡ ጊዜ ፡ እናውቃለን ፡ ብሎ ፡ ከመናገር ፡ ተከልክለው ፡ የሚያገኟቸው ፡ አንክሮ ፡ ተደሞ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ለሀገር ፡ ዘመንኩር ፡ ስማ ፤ ወዘማው ፡ ከዕበ ፡ መንኩር ፡ ትርጓሜ ፡ ምሥጢራቲሃ ።
ስማ ፤ ሥና ፡ ይላል ፤ ስሟ ፤ ብርሃንዋ ፡ ድንቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የምሥጢሯም ፡ ትርጓሜ ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

ኢ ፡ መፍትው ፡ ይዜንዉ ፡ ነገረ ፡ አርምሞ ፡ ዘእልዕቅ ፡ ተወውኮ ።
ልናገር ፡ ልናገር ፡ ማለት ፡ የሌለባት ፡ የአርምሞን ፡ ነገር ፡ ይናገሩት ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ።

ወኢ ፡ ክመ ፡ ይዜንዉ ፡ ተደሞተ ፡ ጎጻርያኒሃ ፡ በርእየ ፡ ስብሐቲው ።
በአርምሞ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጌትነቱን ፡ አይተው ፡ የሚያገኙትን ፡ ተደሞ ፡ ሊናገሩት ፡ አይገባም ።

ወይትመሠጥ ፡ ጎሊናሆሙ ፡ ለእሰ ፡ በውስቴታ ፡ የጎድሩ ።
በአርምሞ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጎሊና ፡ በተ

መሥጠ ፥ ይሔዳል ።

ወይመጠሙ ፥ ንጻርያኒሃ ፥ በእንተ ፥ ተዕመታ ፥ እንተ ፥ ኢትትፈክር ።

ጣዕሚ ፥ የማትመረመር ፥ ስለ ፥ ሆነ ፥ ከአርምሞ ፥ የደረሱ ፥ በባሕረ ፥ አንክሮ ፥ ይሠጥማሉ ።

ናሁ ፥ እንክ ፥ በአርምሞ ፥ ይትአተት ፥ ሕንቃቄ ።

ልናገር ፥ ማለት ፥ እነሆ ፥ በአርምሞ ፥ ይቀራል ።

ወይትከላእ ፥ ተሓባሊ ።

ደፍሬ ፥ ልናገር ፥ የሚል ፥ ይከለከላል ።

ወበልጓመ ፥ ጽግዊ ፥ ይትለጉም ።

በአርምሞ ፥ ልጓም ፥ ይገታል ።

ናሁ ፥ የብሰ ፥ ልሳንየ ፥ እምጽንፀተ ፥ ቍር ፥ ዘጎጣውእየ ።

ከጎጢአቱ ፥ ብርድ ፥ ጽናት ፥ የተነሣ ፥ አንደበቱ ፥ ታሰረ ።

ወኢይክል ፥ ከመ ፥ ይክሥት ፥ ብፅዓን ፥ ዘውስደ ፥ ምሥጢራት ፥ እም ሳክውያት ።

ምሥጢር ፥ የሚገባቸው ፥ የጸድቃንን ፥ ክብር ፥ ገልጸ ፥ ሊናገር ፥ አይችልም ።

በምሕረትከ ፥ እጺወን ፥ ኀበ ፥ አፍቅሮትከ ፥ ከመ ፥ እርከብ ፥ ሣህለከ ፥ እምኀቤከ ።

በፍቅርህ ፥ በምትጸልይልኝ ፥ ጸሎት ፥ ጸጋ ፥ አገኛለኁ ፥ ብዬ ፥ እታመናለኁ ።

አ ፥ መዝገበ ፥ ምሥጢራት ፥ ዘየአምራ ፥ ለብሔረ ፥ ጽግዊ ።

መንግሥተ ፥ ሰማይን ፤ ንጽሐ ፥ ልቡናን ፥ የምታውቃት ፥ የምሥጢራት ፥ መገኛ ፥ ሆይ ።

ወትጸድል ፥ በጸናለ ፥ በብሐቲው ፥ ዘትጺን ፥ ንጻፌ ፥ በብሐቲሃ ፥ ለእለ ፥ ያፈቅርዋ ።

ለሚወዷት ፥ ብርሃንዋን ፥ በምትገልጽ ፥ በጌትነቱ ፥ ብርሃን ፥ የምታበራ ፥ የምሥጢራት ፥ መገኛ ፥ ሆይ ።

ህብ ፥ ሊተ ፥ ጸሎተከ ፥ እንተ ፥ እምሕረትከ ፤ ወለእመኒ ፥ ኮንኩ ፥ ንኪረ ፥ እምን ፥ ብፅዓን ፥ ኢታርሕቀኒ ፥ እምደብረ ፥ ምስካይ ።

በቸርነትህ ፥ ጸልይልኝ ፤ ምንም ፥ አንተን ፥ ለማየት ፥ ባልበቃ ፥ ከልቦናህ ፥ አታርቀኝ ።

ከመ ፥ ኢይርሐቅ ።

ከጌታ ፤ ከመንግሥተ ፥ ሰማያት ፥ እንዳልለይ ።

ወኢይኩን ፥ ሲባየ ፥ ለእሳተ ፥ ዕደም ፥ እንተ ፥ በልዐቶሙ ፥ ለክሓድያን ።

ከሓድያንን ፥ ለምታቃጥላቸው ፥ ለእሳተ ፥ ገሃነም ፥ ምግብ ፥ እንዳልሆን ።

አ ፥ አቡየ ፥ ቅዱስ ፤ አስተበቍዐከ ፥ ዘምስለ ፥ እንብዕየ ፤ ከመ ፥ ትጸሊ ፥ ሳዕሌየ ።

ክቡር ፥ አባት ፥ ሆይ ፤ ትጸልይልኝ ፥ ዘንድ ፥ እያለቀስ ኁ ፥ እለምንኻለኁ ። አንድም ፥ እያለቀስህ ፥ ትጸልይልኝ ፥ ዘንድ ፥ እለምንኻለኁ ።

እበሙ ፥ ርእዩየ ፥ ድኑን ፥ እምጎፍረተ ፥ ምግባርየ ።

የሠራሁትን ፥ ኀጢአቴን ፥ እያሰብኁ ፥ ከማፈሬ ፥ የተነሣ ፥ ራሴን ፥ ደፍቼ ፥ እኖራለኁ ።

ወተለጕመ ፥ ልሳን ፥ ልብየ ፥ እምተናግሮተ ፥ ጎሣግ ፥ ዘተስፋ ፥ ፍቁራን ።

ጻድቃን ፥ እናገኝዋለን ፥ ብለው ፥ ተስፋ ፥ የሚያደርጉትን ፥ ምሥጢር ፥ ከመናገር ፥ አንደበቱ ፥ ተከለከለ ።

አእጋርየኒ ፥ ጸንጸዋ ፥ እምን ፥ ሐዊር ፥ ውስተ ፥ በድው ፥ ኀበ ፥ አልቦ ፥ ምጽላል ።

እግሮቼም ፥ ማረፊያ ፤ መጠጊያ ፥ ወደሌለበት ፥ ምድረ ፥ በዳ ፥ ከመሔድ ፥ የተነሣ ፥ ተሠበሩ ፥ አለ ፤ ተስፋ ፥ ረድኤት ፥ የሌለበት ፥ ሥራ ፥ በመሥራት ፥ አእጋረ ፥ ልቡናዬ ፥ ደከሙ ።

ወቈስላ ፥ እምዕቅፍታተ ፥ እከይ ።

በጎጢአት ፥ በመሰነካከል ፥ ቈሰሉ ።

ወተቀጥቀጣ ፥ እመግግረ ፥ ሐራው ፥ ለርጉም ።

ሰይጣናት ፥ ከሚያሠሯቸው ፥ ከፍትወታት ፤ ከጎጣውእ ፥ የተነሣ ፥ እዳሮቼ ፥ ተሠባበሩ ።

ወናሁ ፥ ርሕቀ ፥ እምኔየ ፥ ብርሃን ፥ አዕይንትየ ፥ በብዝኀ ፥ ሕርትምና የ ።

እነሆ ፥ በጎጢአቴ ፥ ብዛት ፥ የዓይኔ ፥ ዓይን ፥ ክርስቶስ ፥ ከኔ ፥ ራቀ ።

ወኢይክል ፥ ንጽሮቶሙ ፥ ለእሱ ፥ እለ ፥ ዘክርኩ ፥ ለክ ።

አሁን ፥ የጸፍሁልህ ፥ ሀብታት ፥ ምሥጢራትን ፥ ማየት ፥ አይቻለኝም ።

ረሲ ፥ ርጡን ፥ ጸሎትከ ፥ ፈውስ ፥ ለቍስላተየ ።

የጸሎትህን ፥ መድኃኒትነት ፥ ለቍስለ ፥ ኀጢአቴ ፥ መድኃኒት ፥ አድርግልኝ ።

ወኀሊናከኒ ፥ ንቁሐ ፥ ዝግራ ፥ ዘይፌኢ ፥ ሆሎ ፥ የሐውጸኒ ፥ በጊዜ ፥ ሐዘንየ ።

ሁሉን ፥ የሚያውቅ ፤ ለተዘከሮ ፥ ነቅቶ ፥ የሚኖር ፥ ሳሊናሀም ፥ ሐዘን ፥ በመጣብኝ ፥ ጊዜ ፥ ያስበኝ ።

ወይክፍለኒ ፥ ይእዜ ፥ እግዚእን ፥ ከመ ፥ እኩን ፥ ድልወ ፥ ለብፅዓን ፥ ንጽሮትከ ፥ በናትወት ፥ ወበአፍቅሮ ።

ወደኸኝ ፤ ወድጂኽ ፥ አንተን ፥ በማየት ፥ ለሚገኝ ፥ ክብር ፥ እንድበቃ ፥ አድርገኝ ።

እመስ ፥ ኮንኩ ፥ ኀሊ ፥ ዕዉረ ፥ እምዘቲኒ ፥ ካዕበ ።

ዛሬ ፥ አንተን ፥ ከላየኁ ፥ ኋላም ፥ አላይህ ።

ናውኬ ፡ አበድኩ ።
እነሆ ፡ ያላዋቂ ፡ ሥራ ፡ ሠራኁ ።

እንከሰ ፡ ከመ ፡ አብድ ፡ ኢትሕምየኒ ።
ነገር ፡ ዓን ፡ ምነው ፡ ያላዋቂ ፡ አነጋገር ፡ ይናገራል ፡ ብለህ ፡ አትንቀፈኝ ።

እስመ ፡ ጐርውና ፡ ዘዐይነ ፡ ልብከ ፡ ጎሚኒተ ፡ ጎውኣት ፡ ይእቲ ፡ ትክድን ፡ እክያተየ ።
ረቂቁን ፡ ምሥጢር ፡ መርምራ ፡ የምታውቅ ፡ የዐይን ፡ ልቡናህ ፡ ቸርነት ፡ ጎጢአቴን ፡ ትሠውርልኛለችና ፤ አትንቀፈኝ ። አንድም ፡ የዐይን ፡ ልቡናህ ፡ ቸርነት ፡ ረቂቁን ፡ ምሥጢር ፡ የምታውቅ ፡ ናትና ፤ ትክድን ፤ ጎጢአቴን ፡ ትሠውርልኝ ።

መልእክት ፡ ካልኢት ።

ጎበ ፡ አሐጹ ፡ አረጋይ ፡ ቅዱስ ።
ላንድ ፡ አረጋዊ ፡ የጻፉት ፡ ሁለተኛዪቱ ፡ ክታብ ፡ ይህች ፡ ናት ።

አንሰ ፡ አነክር ፡ ሥን ፡ አፍቅሮትከ ፡ እንተ ፡ ትከድናን ፡ እምኵናት ።
የተናቁ ፡ ጎጢአቶቼን ፡ የምትሠውር ፡ መልክዐ ፡ ፍቅርህን ፡ አይቼ ፡ አደንቃለኁ ።

ወኢትረስኦ ፡ እምኔሆን ፡ እለ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ርኩስ ፡ ጸልያን ፡ በእንተ ፡ ርሰዶን ።
የሚያጸይፉ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ይህ ፡ ርኩስ ፡ ዓለም ፡ ከጠላቸው ፡ ከኔ ፡ ጎጣውእ ፡ የተነሣ ፡ እረክሰለኁ ፡ የማትል ፡ ፍቅርህን ፡ አደንቃለኁ ። አንድም ፤ እላ ፡ እለ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ጸልያን ፡ ይላል ፤ ይህ ፡ ዓለም ፡ የጠላቸው ፡ ጎጣውእ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። አንድም ፤ አ ፡ እለ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ጸልያን ፤ አ ፡ እምእሉ ፡ እለ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ጸልያን ፡ ይላል ፡ አብነት ።

ወኮን ፡ ከመ ፡ ዘኢይክል ፡ ተወግሦ ፡ ጎጻፌ ፡ ጲአቶን ።
ክፉ ፡ መዓዛቸውን ፡ መታገሥ ፡ እንደማይቻለው ፡ የሆነ ፤ ይህ ፡ ዓለም ፡ የጠላቸው ።

ወልዑኒ ፡ ዘንፋቅ ፡ ጎደነን ፡ ወገደፍን ፡ እምኔሁ ፡ ለድጎር ፡ ከመ ፡ ኢይርኩስ ፡ ቦን ።
ልቡናው ፡ የሚጠራጠርም ፡ ሰው ፡ ያረከሱኛል ፡ ብሎ ፡ ተጸየፋቸው ።

ፀኑ ፡ እመ ፡ ልብከ ፡ ዘኢወረደ ፡ እምሀገር ፡ ዘሱጎሌ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ጎበ ፡ ፀቢዖ ፡ ንጉሥ ።
የኔን ፡ ጎጢአት ፡ አለ ፡ መጸየፍህ ፡ በውኑ ፡ ልቡናህ ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ከምታደርግ ፡ ከንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ባይወርድ ፡ ነው ፤ ባይወርድ ፡ እንጂ ፡ ነው ፤ ወይም ፡ እንጂ ፡ ባይወርድ ፡ ነው ።

ወበእንተዝ ፡ ኢያአመራ ፡ ለወገረ ፡ ጽልመት ።
ከንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ድንቁርናን ፡ ጎጢአትን ፡ በያውቃት ፡ እንጂ ፡ ነው ።

ወኢሰበወ ፡ ሑረታ ፡ ጸላመ ።
ክፉ ፡ አናወጧን ፡ በያውቅ ፡ ነው ፤ በያውቅ ፡ እንጂ ፡ ነው ።

እሙ ፡ ይከውንሁ ፡ ዘንሥኣ ፡ ሎቱ ፡ ምሳሌ ፡ እምን ፡ አርኣያሁ ፡ ለፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡ ዘኅለጣት ።
የጻድቃን ፤ የመላእክት ፡ ዕውቀት ፡ ከሚሆን ፡ ከጌታ ፡ ጻብር ፡ አለ ፡ መለያየትን ፡ አብነት ፡ ቢያደርግ ፡ ነው ፤ አብነት ፡ ቢያደርግ ፡ እንጂ ፡ ነው ፤ ወይም ፡ እንጂ ፡ አብነት ፡ ቢያደርግ ፡ ይሆናል ።

ዘያሠርቅ ፡ ጸዳሎ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ይንብሩ ።
በመከራ ፡ ላሉ ፡ ረድኤትን ፤ በድንቁርና ፡ ላሉ ፡ ዕውቀትን ፡ የሚገልጽ ፡ ብሎ ፡ ለጌታ ፡ ቀደለ ።

ወለእመ ፡ ከንኩ ፡ ዘኢይትከሀለኒ ፡ እዕሚከ ፡ በእንተ ፡ ጸጋ ፡ ዘጸነከ ፡ ላፅለ ፡ እከይደ ፤ ሀለመ ፡ ባሕቱ ፡ አምላክ ፡ ጐር ፡ ውእቱ ፡ ይዕሚክ ፡ በምግባሩቲሁ ።
ጎየእ ፡ ነህ ፡ ሳትል ፡ ስለ ፡ ወደድኸኝ ፡ የፍቅርህን ፡ ዋጋ ፡ እመልስ ፡ ዘንድ ፡ ባይቻለኝ ፡ በቸርነቱ ፡ ዋጋህን ፡ የሚሰጥህ ፡ ቸር ፡ አምላክ ፡ እንጂ ፡ አለ ፤ እሱ ፡ ዋጋህን ፡ ይስጥህ ።

ወየሀብክ ፡ ዅሎ ፡ ሀብታተ ፡ ዘትፈትዖሙ ፡ ንፍስከ ።
ሰውነትህ ፡ የምትሻቸዉን ፡ ሀብታት ፡ ይስጥህ ።

እለ ፡ ፍትወታቲሆሙ ፡ እንተ ፡ ኢተጎልፍ ።
ፍቅራቸው ፡ የማትሰለች ።

አሜን ።
ይሁንልን ፤ ይደረግልን ።

ታዜክረኒኑ ፡ ከመ ፡ ኢይርሳዕከ ፡ ለዘኢትትረሳዕ ።
በሥላሴ ፤ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ የማትረሳ ፡ አንተን ፡ እንዳልረሳህ ፡ አትርሳኝ ፡ ትለኛለህን ።

እስመ ፡ ብከ ፡ እለ ፡ ይናዝዙከ ።
የሚያጠኑህ ፡ መላእክት ፤ ደስ ፡ የሚያሰኙህ ፡ ሀብታት ፡ ምሥጢራት ፡ ሳሉህ ፡ አትርሰኝ ፡ ትለኛለህን ።

ወእንሰ ፡ ስሑት ፡ ዘበአማን ።
እኔ ፡ በውነት ፡ ጎየእ ፡ ስሆን ።

ወዘይእዜሰ ፣ ማኅደርከ ፣ ድኩም ፣ ፈድፋደ ።
ዛሬ ፣ ያለህበት ፣ ዓለም ፣ ጎላፈ ፣ ነው ። አንድም ፣ ዛሬ ፣ ያለህበት ፣ ሥጋ ፣ ፈጽሞ ፣ ደካማ ፣ ነው ።

አላ ፣ ጎበ ፣ ዝኩሰ ፣ ማኅደር ፣ ዘይዔውው ፣ ልበ ፣ በዔዋዊሁ ።
በፍቅሩ ፣ ልቡናን ፣ የሚማርክ ፣ የወዲያኛዉን ፣ ዓለም ፣ አናወር ፣ አስብ ፣ እንጂ ።

ወእነሂ ፣ እኮ ፣ ዘእመሰዪ ፣ ሥጋ ፣ ጸዐሮ ፣ እቤለክ ።
እኔም ፣ ስሑት ፣ ነኝ ፣ ብዬ ፣ እንደ ፣ ነገርሁህ ፣ ከነጽሮ ፣ ደርሼ ፣ በመረዳት ፣ የማውቀው ፣ አይደለም ።

አላ ፣ ባሕቱ ፣ አእምን ፣ ክመ ፣ ይትወሀብ ፣ ለክ ፣ ፍትወታቲክ ።
የምትሻቸው ፣ ሀብታት ፣ እንዲሰጡህ ፣ አምናለኁ ፣ እንጂ ።

እዘመ ፣ ዝንቱ ፣ ውእቱ ፣ ቃሉ ፣ ለዘአሰፈወ ፣ ክመ ፣ ኢይንድፍ ፣ ፍትወቶ ፣ ለፈታዊ ፣ ወናያት ።
በጎ ፣ ነገር ፣ ለሚሻ ፣ ሰው ፣ የሚሻዉን ፣ እንዳይነሣው ፤ ሰአሉ ፣ ወይትወሀበክሙ ፣ ብሎ ፣ የተናገረው ፣ ነገሩ ፣ ይህ ፣ ነውና ።

ኢትክል ፣ የማንየ ፣ ክመ ፣ ትሥዐል ፣ አምሳሊሁ ፣ ለሠዓሴ ፣ ሎሱ ።
ሁሉን ፣ የፈጠረ ፣ የጌታን ፣ መልክ ፣ በጽሕፈት ፣ ትገልጽ ፣ ዘንድ ፣ ለቀኝ ፣ እጇ ፣ አይቻላትም ።

አልፅል ፣ ጎሊናክ ፣ እምንጽሮተ ፣ ምስላት ።
ሥነ ፣ ፍጥረትን ፣ ከማየት ፣ ጎሊናህን ፣ ለየው ።

ወአእትት ፣ ሎሱ ፣ እምቅድመ ፣ አዕይንቲከ ።
ሁሉንም ፣ ከፈትህ ፣ እንደሌለ ፣ አድርገው ።

ወንጽር ፣ ጎበ ፣ ባሕቲቱ ።
እሱን ፣ ብቻ ፣ አስብ ።

ብፁዕ ፣ ዘአእተተ ፣ እምቅድሜሁ ፣ ሎሱ ፣ ራእያተ ፣ ምድር ፣ ወሳላቲ ።
ከፈቱ ፣ ምድራዊ ፣ ጓጉርን ፣ ያራቀ ፣ ንፁድ ፣ ክቡር ፣ ነው ። ወሳዲቱ ፣ አለ ፤ በአጸም ። አንድም ፣ በቁመ ፣ እናቱን ፣ የተወ ፣ ሰው ፣ ንፁድ ፣ ክቡር ፣ ነው ። ዘም ድረ ፣ ለብሰ ፣ እንዲል ።

ወተወልያተ ፣ ነፍሱስ ፣ ምክዕቢተ ፣ ይክውኖ ።
ኃላ ፣ የሚገኝ ፣ ክብር ፣ እጽፍ ፣ ሁኖ ፣ ይሰጠዋል ።

ሑረቱ ፣ ይረትዕ ፣ መንገስ ፣ ምሥጢር ።
ከዚያ ፣ አስቀድሞ ፣ ዛሬ ፣ ምሥጢር ፣ በመመርመር ፣ አናዋሩ ፣ የቀና ፣ ይሆናል ።

ዘይገብር ፣ መንክሬተ ፣ ይመሥጥ ፣ ልቦሙ ፣ ለእለ ፣ የሐውሩ ፣ በብርሃን ፣ እግዚአብሔር ።
አንክሮን ፤ ተደሞን ፣ የሚያደርግ ፣ ሰው ፣ ከአግዚአብሔር ፣ በሚገኘው ፣ ዕውቀት ፣ ጸንተው ፣ የሚኖሩ ፣ ሰዎችን ፣ ልቡና ፣ ጠልፎ ፣ ይወስዳል ፤ ማለት ፤ ደስ ፣ ያሰኛል ።

ሀገር ፣ ጽሬት ፤ ወሠናይት ፣ አይቴ ፣ ህለወት ።
ንጽሐ ፣ ልቡና ፤ መንግሥተ ፣ ሰማያት ፣ ወዴት ፣ አለች ፣ ብለው ።

ናሁ ፣ ጎስፈ ፣ ሎሱ ፣ እምቅድመ ፣ ገጽየ ፣ ወእግዚአ ፣ ሎሱ ፣ ባሕቲቱ ፣ ያስተርእየኒ ።
እነሆ ፣ ሁሉ ፣ ከፊቴ ፣ ተሠወረ ፤ እንዳልነበረ ፣ ሆነ ፤ ጌታ ፣ ብቻ ፣ ይታየኛል ። ንጽሐ ፣ ልቡና ፤ መንግሥተ ፣ ሰማያት ፣ ወዴት ፣ አለች ፣ ብለው ።

ኢየአምር ፣ ጎበ ፣ ህሎኩ ፣ አነ ።
እኔስ ፣ ያለሁበትንም ፣ አላውቅም ፣ አለኝ ።

እስመ ፣ ተዔወወ ፣ ልብየ ፣ በሥነ ፣ ራእያት ።
ልቡናዬ ፣ ጌታን ፣ በማየት ፣ ተማርኳልና ።

ብፁዕ ፣ ውእቱ ፣ ዘተሐቅረ ፣ ምስሌክ ፣ ወኖመ ።
ካንተ ፣ ጋራ ፣ ተውሕዶ ፣ ከመከራ ፣ ያረፈ ፣ ሰው ፣ ንውድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ወዘእዜነው ፣ መዓዛከ ፣ ፍትው ።
የተወደደ ፣ መዓዛህን ፣ ያሸተተ ፣ ንውድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ብፁዕ ፣ ውእቱ ፣ ዘነበረ ፣ ወርእየ ፣ ሠራቆተክ ፣ እንዘ ፣ ትትወሐድ ፣ በቱ ፣ ክመ ፣ ጸዳለ ፣ ፀሐይ ፣ በውስተ ፣ ክበቡ ።
ብርሃነ ፣ ፀሐይ ፣ ከክበቡ ፣ እንዲዋሐድ ፣ ተውሕዶኸው ፣ ስትገለጽ ፣ ብርሃንህን ፣ በማየት ፣ የኖረ ፣ ሰው ፣ ንውድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ብፁዕ ፣ ውእቱ ፣ ዘደሬኢ ፣ ተሌስዮቶ ፣ እንዘ ፣ ይትዌለጥ ፣ ጎበ ፣ አም ሳሊክ ።
ምግቡን ፣ አንተን ፣ ወደ ፣ መምሰል ፣ ሲለወጥ ፣ ያየ ፣ ሰው ፣ ንውድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ወይሰልየ ፣ እንዘ ፣ ኢየአምር ፣ በእንተ ፣ አስተሐውዞትክ ፣ ዋዕምት ።
አንክሮህ ፣ ደስ ፣ የሚያሰኝ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ሳያውቅ ፣ የሚመገበው ፣ ብፁዕ ፣ ነው ።

ብፁዕ ፣ ዘይሬእየክ ፣ ቱሱሐ ፣ ውስተ ፣ ስቱሁ ፣ ወይሰትየክ ።
በመጠጡ ፣ ተውሕደህ ፣ የሚያይህ ፣ አንተን ፣ መጠጥ ፣ ያደረገ ፤ ማለት ፤ ሲጠጣ ፣ የሚያስብህ ፣ ሰው ፣ ንውድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ወይትፈሣሕ ፣ ልቡ ፣ በአፍቅሮትክ ።
ልቡ ፣ በፍቅርህ ፣ ደስ ፣ የሚለው ፣ ሰው ፤ ብፁዕ ።

ብፁዕ ፣ ውእቱ ፣ ዘፀእከ ፣ ውስተ ፣ ልቡ ፤ ወይፈእየክ ፣ በመንክር ፣ ራእይ ፤ ወያነክር ፣ ሥነክ ፣ ፍትው ፣ ዘይፈለፍል ፣ እምውሳጤሁ ።

በልቡ ፡ ያደርሀበት ፤ በድንቅ ፡ አተያየት ፡ የሚያይ ሀ ፤ በልቡ ፡ የሚታሰብ ፡ የተወደደ ፡ መልክህን ፡ የ ሚያነክር ፡ ሰው ፡ ንፁድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

ናሁ ፡ ተቁጥፀ ፡ ልብየ ፡ ሳዕለ ፡ ኀለት ፡ ከመ ፡ እስብራ ።

እነሆ ፡ የምጽፍበትን ፡ ብር ፡ ስበራት ፡ ስበራት ፡ አለ ኝ ።

እስመ ፡ ኢይትክሀሳ ፡ ትሥዕል ፡ ሊተ ፡ በዝየ ፡ አምሳሊሁ ፡ ለንኩረ ፡ ሥን ፡ ዘእን ፡ እፈእዮ ።

እኔ ፡ የማየው ፤ መልኩ ፡ ያማረ ፤ የተወደደ ፡ የጌታ ን ፡ መልክ ፡ ጽፋ ፡ ማሳየት ፡ አይቻለትምና ።

አፍላን ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ ኢለ ፡ ይውሕዝ ፡ እምእንቅፅተ ፡ ብዕኅን ፡ ሶ በ ፡ ይሠርቁ ፡ ይከይኑ ፡ ለአስተራምሞ ።

ከሥላሴ ፡ የሚሰጡ ፡ ሀብታት ፡ ምሥጢራት ፡ በተገለ ጹ ፡ ጊዜ ፡ ገዛም ፡ ያሰኛሉ ።

ወያፈርሁ ።

ያበርሁ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ብሩህ ፡ ያደርጋሉ ።

ኢትሕምዮ ፡ ለገዝንጋኤየ ።

ገዝንጉ ፡ ሰውነቱን ፡ አትንቀፈው ።

ናሁ ፡ ተዳደቀኒ ፡ በገዘ ፡ ስካረ ፡ ወይን ፡ ዘያሰተፈሥሕ ፡ ሠሎ ።

ሁሉን ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኝ ፡ የወይን ፡ ስካር ፡ አንክ ሮ ፡ ተደሞ ፡ ያዘኝ ።

መረሳዕክሞ ፡ ለንፍስየ ።

ሰውነቱን ፡ ዘንጋኢት ።

ሠሎ ፡ ልብ ፡ ዘያሰዝን ፡ ነቢብ ፡ ዕበ ፡ ይበውእ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ይትለጉም ፡ እምነቢብ ።

ብዙ ፡ ነገር ፡ ይናገር ፡ የነበረ ፡ ልብ ፡ ከንጽሐ ፡ ልቡ ና ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ዐውቃለኁ ፡ ብሎ ፡ ከመናገር ፡ ይ ከለከላል ።

ወያረምም ፡ እምን ፡ ሁከታተ ፡ እንዘሮ ፡ ዘምሥጢራት ።

ምሥጢራትን ፡ እያየ ፡ ከማንከር ፡ ሁከት ፡ የተነሣ ፡ ዝም ፡ ይላል ።

በገዘ ፡ ያርኢ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥኖ ፡ ለፍቱራኒሁ ።

ዘንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከንጽሮ ፡ ለ ደረሱ ፡ ወዳጆቹ ፡ መልኩን ፡ ይገልጽላቸዋል ።

በገዘ ፡ ትፌኢ ፡ ነፍስ ፡ ህላዌ ፡ ርእሳ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ አካሷን ፡ ታያለች ።

ወለክርስቶስኒ ፡ ዘጎዳር ፡ ውስቴታ ፡ እንዘ ፡ ይሠርቅ ።

በርሷ ፡ አደሮ ፡ ያለ ፡ ክርስቶስንም ፡ ሲያበራ ፡ ታየዋ ለች ።

ወያጸድሳ ፡ በርእየ ፡ ጸዳሉ ።

ብርሃኑን ፡ በማየት ፡ ብርሀት ፡ ያደርጋታል ።

በገዘ ፡ ህለወ ፡ ሥናሙ ፡ ለመላእክት ፡ መንፈሳውያን ፡ እንዘ ፡ ያንክ ሩ ፡ ወይሴብሕዎ ፡ ለማሕየዊ ፡ ዓለማት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ረቂቃን ፡ መላእክት ፡ የዓለማት ፡ መገ ኛ ፡ ጌታን ፡ ሲያመሰግኑ ፤ ሲያነክሩ ፡ መልክቸውን ፡ ታያለች ።

በገዘ ፡ ይትረአይ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ሦስትነት ፡ ይታያል ።

በምሥጢር ፡ ወበጎሲና ፡ ለተናገዘ ፡ ዮስቲርኢ ፡ አካላቲሁ ።

ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ አክሉ ፡ በንዮነት ፡ በሦስትነት ፡ ይ ታያል ።

ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ ገንቱ ፡ ምሥጢር ።

ይህ ፡ ምሥጢር ፡ ረቂቅ ፡ ነው ።

ወለጎሲና ፡ ጽሩይ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይትረአይ ።

ለበቃ ፡ ሳሊና ፡ ብቻ ፡ ይገለጻል ፡ እንጂ ።

በገዘ ፡ ያስተርኢ ፡ ኅለም ፡ ዘህለም ፡ ይምጻእ ፡ ለእለ ፡ ቀተሉ ፡ ነፍሶ መ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ በውሳጤ ፡ ልቦሙ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ብለው ፡ መከራ ፡ ለ ተቀበሉ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ መንግሥተ ፡ ሰ ማያት ፡ በዓይነ ፡ ልቡናቸው ፡ ይታያል ።

በውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለሊሁ ፡ ኅለመ ፡ ኅለማት ።

ይኸውም ፡ የጻድቃን ፤ የመላእክት ፡ ዓለም ፡ የሚሆ ን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ያስተርኢ ፡ ክሣኖ ፡ ኅለመ ፡ ሐዲስ ፡ ፈጣሬ ፡ ኅለማት ፤ ሀገሬታ ፡ ለፍ ጥረት ፡ ነባቢት ።

የነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ከተማዋ ፡ የሚሆን ፤ ዓለማትን ፡ የ ፈጠረ ፡ ጌታ ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ ሁኖ ፡ ይታያል ።

መብልዓኒ ፡ ውእቱ ፡ በቱሃኒ ።

መብሏም ፡ መጠጧም ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወፍሥሓሃኒ ፡ ፀሐያ ።

ደስታዋም ፡ ማየታ ፡ ነው ።

ወፀሐያኒ ፡ ልብሳ ።

ማየታም ፡ ተዋሕዶዋ ፡ ነው ።

ወልብሳኒ ፡ ውእቱ ፡ ሕሴታ ።

ተዋሕዶዋም ፡ ባለ ፡ ሚልኒቲ ፡ ነው ።

ወሕሴታኒ ፡ አእምሮታ ።

ባለ ፡ ሚልኒቲም ፡ ማየታ ፡ ነው ።

ወአእምሮታኒ ፡ አርኣያሃ ።

ማየታም ፡ መልኳ ፡ ነው ።

ወአርኣያሃኒ ፡ ራእየ ፡ ጸጋሃ ።

መልኳም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ነው ።

ፍጥረት ፡ በፈጣሪሃ ፡ ትፌእሶ ፡ ለፈጣሪሃ ፡ ከዊኖ ፡ አክለ ፡ ቆማ ።

ፍጥረት ፡ ፈጣሪዋን ፡ በቁመቷ ፡ ልክ ፡ ሁኖ ፡ ታየዋለች ፤ ማለት ፤ በከበበ ፡ ትስብእት ፡ ታየዋለች ። እንድም ፡ ፈጣሪዋን ፡ አካሏ ፡ ጠርቶላት ፡ በአካሏ ፡ ታየዋለች ።

ወኮሱ ፡ ዘይረክቦን ፡ ለእላ ፡ ይረክባ ፡ ለትንግኤ ፡ እንተ ፡ ትቀድም ፡ መጺአ ።

እሊሀን ፡ ሀብታት ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ሁሉ ፡ አስቀድማ ፡ የምትሰጥ ፡ ትንግኤ ፡ ልቡናን ፡ ያገኛታል ።

ወኮሎሙ ፡ እለ ፡ ደለዎሙ ፡ ዝንቱ ፡ ኢያስተርእዩ ፡ ምስለ ፡ ምውታን ።

ከዚህ ፡ ማዕርግ ፡ የደረሱ ፡ ሁሉ ፡ ከጎዮአን ፡ ጋራ ፡ አይቈጠሩም ።

መልእክት ፡ ግልሲት ።

ኀበ ፡ አሐዱ ፡ እጎ ፡ ዘክን ፡ ያፈቅሮ ፤ ወእምዝ ፡ ገነየ ፡ ለስይጣን ፡ ወእንዘ ፡ ለአረጋዊ ፡ ይጽርፍ ፡ ሳዕሌሁ ።

ቀድሞ ፡ ይወደው ፡ ለነበረ ፤ ኋላ ፡ ለሰይጣን ፡ ተገዝቶ ፡ አረጋዊን ፡ ይነቅፍ ፡ ዘንድ ፡ ለዝመረ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ የጻፋት ፡ ሦስተኛዪቱ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ናት ።

ወይቤ ፤ እንስ ፡ እትፈሣሕ ፡ ፈድፋደ ፡ ዖበ ፡ ትሔምየኒ ፡ ወትጼዕደኒ ።

ብታማኝ ፤ ብትነቅፈኝ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

እኁልቆ ፡ እን ፡ ከመ ፡ ዘበቍጌት ።

ስድቡን ፤ ነቀፋዉን ፡ ከምስጋና ፡ እቈጥረዋለኁ ፤ እንደ ፡ ክብር ፡ አየዋለኁ ።

አላ ፡ አንተስ ፡ ትብለኒ ፡ ዖበ ፡ እጼዕሎ ፡ ለምንት ፡ ይትኤገሠኒ ።

አንተ ፡ ሳን ፡ ስሰድበው ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ይለኛል ፡ ቢንቀኝ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ትለኛለህ ።

ለማዕ ፡ ይእዜ ፡ ዘእነግረከ ።

የምነግርህን ፡ ስማ ።

ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ብየ ፡ ጥምቀት ፡ ዘእጠመቅ ፤ ወሀለዉኒ ፡ እፈጽማ ።

ጌታችን ፡ የምጠመቀው ፡ ጥምቀት ፡ አለኝ ፤ እፈጽማትም ፡ ዘንድ ፡ አለኝ ፡ ብሏል ።

ዘውእቱ ፡ እንስ ፡ ድልው ፡ ለሞት ፤ ወእጸንሕ ፡ መታሰረ ።

ይኸውም ፡ ብየ ፡ ጥምቀት ፡ ያለው ፡ እሞታለኁ ፤ እ ፈጽማ ፡ ያለው ፡ እቀበራለኁ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወባሕቱ ፡ እኮ ፡ መፍትው ፡ ለይሁዳ ፡ ፍቁሩ ፡ ከመ ፡ ያግብኦ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የጌታ ፡ ሞቱ ፡ ምንም ፡ በፈቃዱ ፡ ቢሆን ፡ ለወዳጁ ፡ ለይሁዳ ፡ ጌታን ፡ ሊያሲዘው ፡ በልተገበጠም ፡ ነበር ። እንድም ፤ ያግብኦ ፡ ለፍቁሩ ፡ ብለህ ፤ ወዳጁን ፡ ጌታን ፡ ያሲዘው ፡ ዘንድ ፡ ለይሁዳ ፡ ባልተገባውም ፡ ነበር ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ መሰደቡ ፡ ምንም ፡ የኔ ፡ ፈቃድ ፡ ቢሆን ፡ ወዳጅህን ፡ እኔን ፡ ልትሰድበኝ ፡ ባልተገባህም ፡ ነበር ። እንድም ፡ በይሁዳ ፡ በል ፤ ምንም ፡ የጌታ ፡ ሞቱ ፡ በፈቃዱ ፡ ቢሆን ፡ ያሲዘው ፡ ዘንድ ፡ በወደደው ፡ በይሁዳ ፡ ፍዳ ፡ አልቀረበትም ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ መሰደቡ ፡ ለኔ ፡ ምንም ፡ ፈቃዴ ፡ ቢሆን ፡ ፍዳ ፡ እንጂ ፡ አይቀርልህም ።

መልእክት ፡ ራብዒት ።

ስምክሰ ፡ እ ፡ እጉየ ፡ ዐቢይ ፡ እምስመ ፡ ዘመድክ ።

አራተኛዪቱ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ናት ። ወንድሜ ፡ ስምህ ፡ ከመላእክት ፡ ስም ፡ ይበልጣል ። ዘመድከ ፡ አለ ፤ በተፈጥሮ ። አንድም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ሚካኤል ፡ ይባላል ፤ ያለቃቸው ፡ ስም ፡ ነውና ። አንድም ፡ ከመነኰሳት ፡ ስም ፡ ይበልጣል ፡ አለ ፤ አበ ፡ ምኔት ፡ ነውና ። አንድም ፡ ከሰብአ ፡ ዓለም ፡ ይበልጣል ፤ ሕዝባዊ ፡ ከመበል ፡ መነኰሴ ፡ መባል ፡ ይበልጣልና ። አንድም ፡ ከኢጥሙቃን ፡ ይበልጣል ፤ አረሚ ፡ ከመበል ፡ ክርስቲያን ፡ መባል ፡ ይበልጣልና ። አንድም ፡ ከእንስሳት ፡ ስም ፡ ይበልጣል ። ዘመድከ ፡ አለ ፤ በተፈጥሮ ፤ እንስሳ ፡ ከመበል ፡ ሰው ፡ መባል ፡ ይበልጣልና ።

ለይኩንኬ ፡ ሥርዓትከ ፡ ዘይትማሰል ፡ በተሰምዮትከ ።

ግብርህም ፡ እንደ ፡ ስምህ ፡ ይሁን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥጋከ ፡ ብሩህ ፡ በንጽሕና ።

ሰውነትህ ፡ በንጽሕና ፡ ብሩህ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

በከመ ፡ እልክቱኒ ፡ ጽሩያን ፡ በንጽሕናሆሙ ፤ ወንፍስኒ ፡ ከማሁ ፡ ጽሬተ ፡ ለትኩን ፡ እምኀሲና ፡ ዘሕግም ።

መላእክት ፡ በንጽሕናቸው ፡ ብሩሃን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ነፍስህም ፡ ከኀልዮ ፡ ኀጢአት ፡ የተለየች ፡ ትሁን ።

በከመ ፡ እሙንቱኒ ፡ እሳት ፡ ዘይነድድ ፡ በንጽሮ ፡ ዘዘልፍ ፡ ኀበ ፡ እግ

ዚአብሔር ፤ ክማሁ ፡ ይኩን ፡ ንጻፌክ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕጸት ።
መላእክት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመዘክ
ር ፡ እንደሚቃጠል ፡ እሳት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፤ እንደዚህ
ም ፡ ሁሉ ፡ እሱን ፡ መዘከርህ ፡ ያለ ፡ መለየት ፡ ይሁን ።

ከመ ፡ ትንግኢ ፡ ነፍስከ ፡ አምሳሊሆሙ ።
ሰውነትህ ፡ መላእክትን ፡ ትመስል ፡ ዘንድ ።

አጽዕቅ ፡ ላዕለ ፡ ነፍስከ ፡ በኀጢአ ፡ ቢሳይ ።
ሰውነትህን ፡ ምላብ ፡ ነሥተህ ፡ በረኃብ ፡ አስጨንቃ
ት ።

ወእምነገረ ፡ በብእ ፡ ፍጹመ ፡ ተገንሥ ።
ከሰው ፡ ነገር ፡ ፈጽመህ ፡ ተከልከል ።

እምከልእኒ ፡ ግብር ፡ በብዙኅ ፡ ተዐቅበ ።
ከሌላውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ ተዐቅበ ፡ ሁኔህ ፡
ተለይ ።

ከመ ፡ ታጥፍእ ፡ ላህፀ ፡ ፍትወት ፡ ምንኀት ፡ እምላዕሌከ ።
የተናቀች ፡ የፈቲውን ፡ ጸር ፡ ከንተ ፡ ታጠፋት ፡ ዘን
ድ ።

ወእሱ ፡ እሙንቱ ፡ ዕፀዊሁ ፡ ለዘይትቃረኑ ፤ ወይትጋደል ፡ ምስሌን ፤
ወበሙ ፡ ያንድድ ፡ እሳቶ ፡ በዘያውዕየን ።
በሚጐዳን ፡ ገንዘብ ፤ ይጐዳን ፡ ዘንድ ፡ ጸሩን ፡ የሚ
ያጸናባቸው ፤ የሚጣላን ፤ የሚዋጋን ፡ የሰይጣን ፡ ም
ክንያቶቹ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

ተናግሮ ፡ ምስሉ ፡ ሕዝባውያን ፤ ወተዋህቶ ፡ ምስሉ ፡ አንበት ።
ከምክንያቶቹም ፡ አንዱ ፡ ከበላ ፡ ነጮች ፡ ጋራ ፡ መ
ጨዋወት ፤ ከሌቶች ፡ ጋራ ፡ ግር ፡ ግር ፡ ማለት ፡ ነ
ው ።

ወፍቅረ ፡ ወራዙት ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ውስደ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፤ እሙ ፡ ደ
ቂቅክ ፡ ዘታሕተ ፡ ትእዛዝከ ።
ዓለማውያንም ፡ ቢሆኑ ፤ ተሹመህባቸው ፡ ያሉ ፡ አር
ድእትህም ፡ ቢሆኑ ፡ ሕፃናትን ፡ መውደድ ፡ ነው ።

እሱ ፡ ያፈደፍዱ ፡ እምሰሉ ፡ እክያት ፡ ለተፃርኖተ ፡ ሐረሳዊ ፡ ዘክርስቶ
ስ ።
የክርስቶስ ፡ ገበሬ ፡ ከሚሆን ፡ ከባሕታዊ ፡ ጋራ ፡ ለ
መዋጋት ፡ ከጎጣውእ ፡ ይልቅ ፡ እሊህ ፡ ጸሩን ፡ ያጸ
ናሉ ።

ወዕበ ፡ ይመጽኣ ፡ ዐርክት ፡ መናፍቃት ፡ ዘውእቶን ፡ መንኰሳይያት ።
ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ የሚለዩ ፡ ሕፃናት ፤ መ
ንኰሳይያት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ከነዚያ ፡ ጋራ ፡ መጨዋ
ወት ፡ ነው ።

ወእሙንሰ ፡ ለእላንቱ ፡ ደቂቀ ፡ አፍያት ፡ ጕርጌ ፡ ይእቲ ።
የፍኝት ፡ እባብ ፡ ልጆች ፡ እናታቸው ፡ የምትሆን ፡ የ
ሊህ ፡ ጎጣውእ ፡ ምክንያታቸው ፡ እበላ ፡ ማለት ፡ ነ
ው ። አንድም ፤ አመ ፡ ትመጽእ ፡ ምስለ ፡ ዐርክት ፡
ይላል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ የሚለዩ ፡ መን
ኰሳይያትን ፡ አስከትላ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ ለነዚህ ፡ ጎ
ጣውእ ፡ ምክንያት ፡ የምትሆን ፡ ቀባጣሪ ፡ እመ ፡ ም
ኔት ፡ ናት ።

ወተዐርኮቶሙ ፡ ለእንው ፡ ዕሩኃን ፡ እለ ፡ ይትህከዩ ፡ ግብረ ፡ ሕይወቶ
ሙ ።
የሰይጣን ፡ ጸሩ ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ሕይወት ፡ የሚያ
ገኙበትን ፡ ሥራ ፡ ቸል ፡ የሚሉ ፡ አጎውን ፡ ወዳጅ ፡
ማድረግ ፡ ነው ።

ለእመ ፡ ተዐርቀት ፡ ነፍስነ ፡ እምነ ፡ እሱ ፡ አልባቲ ፡ በዘትወድቅ ፡ ው
ስተ ፡ መሣገፊሁ ፡ ለዘይትጋደል ፡ ምስሌን ።
ሰውነታችን ፡ ከሊህ ፡ ጎጣውእ ፡ የተለዩች ፡ እንደ ፡ ሆ
ነ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ በሚዋጋ ፡ በሰይጣን ፡ አሽከላ ፡ በም
ትያዝ ፡ ገንዘብ ፤ የምትያዝበት ፡ የለም ።

ወፍሙን ፡ ይትህሀስ ፡ ስፈር ፡ ንበ ፡ እግዚአብሔር ።
እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈጥነን ፡ ከእግዚአብሔ
ር ፡ ጋራ ፡ መዋሐድ ፡ ይቻለናል ።

ወፀቱ ፡ ጎድጎን ።
በመዋሐዳችን ፡ ከጸሩ ፡ እንድናለን ።

ወከዕበ ፡ ዝንቱ ፡ ሥጋነ ፡ ይረስዕ ፡ ዘሎቱ ።
ዳግመኛ ፡ ይህ ፡ ሰውነታችን ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃዱን ፡ ይ
ዘነጋል ።

ዘውእቶን ፡ ፍትወታቲሁ ፡ ርኩሳት ።
እሊሁም ፡ ሊሠራቸው ፡ የሚወድ ፡ ጎጣውእ ፡ ናቸ
ው ።

ወሶበ ፡ ይትከላእ ፡ እምነ ፡ እላንቱ ፡ ለእመ ፡ ተሀውክ ፡ ካዕበ ፡ እምገ
ዕዝ ፡ ጠባይዕ ፡ ውስቴቱ ፡ ይጠፍእ ፡ ዘእንበለ ፡ ጸግ ።
ከሊህ ፡ ተከልክሎ ፡ ሳለ ፡ የባሕርይ ፡ ጸር ፡ ቢነሣበት ፡
ሳያስቸግረው ፡ ይጠፋለታል ።

እ ፡ እጉየ ፡ አስተበቁዐከ ፡ አነ ፡ ፍቁርከ ፡ ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ እሶንተ ፡
ተግግፃተ ።
ወንድሜ ፤ እሊህን ፡ ትእዛዝት ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ወ
ዳጅኽ ፡ እኔ ፡ እማልድኻለኁ ።

እስመ ፡ ሥርኅት ፡ ዘእንቲኣን ፡ ኢኮነት ፡ በከ ።
የኛ ፡ ሥራት ፡ ዋጋ ፡ የማታሰጥ ፡ አይደለችምና ።

አላ ፡ አርኣያ ፡ መላእክት ፡ ልዑላን ፡ ይእቲ ።
መላእክትን ፡ የምታስመስል ፡ ናት ፡ እንጂ ።

አብዝኖ ፥ ንዋም ፥ ያጸልም ፥ ልበ ።
አንቅልፍ ፥ ማብዛት ፥ አእምሮን ፥ ይለውጣል ።

ከመ ፥ ኢይፍልጥ ፥ እሱንተ ።
አሊሀን ፥ ሀብታት ፥ ለይቶ ፥ እንዳያውቅ ።

ለእመ ፥ ተጋህክ ፥ ትከውን ፥ ሱታፊሆሙ ፥ ለሱራፌል ።
ተሳተ'ኸ ፥ ሥራ ፥ ብትሠራ ፥ ሱራፌልን ፥ ትመስላቸ ዋለህ ።

ወትረክብ ፥ ጉባዔ ፥ ዘይኄይስ ፥ እምሱታፌ ፥ ሰብእ ።
ከሰው ፥ ጋራ ፥ አንድ ፥ በመሆን ፥ ከምታገኘው ፥ የሚ በልጥ ፥ ጸጋን ፥ ታገኛለህ ።

ፍቅረ ፥ እግዚአብሔርኒ ፥ ወትረ ፥ ይነድድ ፥ በውስቴትክ ፥ በእምጣነ ፥ ሀልዎቶን ፥ ለሕግማት ፥ ዲበ ፥ ነፍስክ ።
ኀጣውኢ ፥ በሰውነትህ ፥ የኖሩ ፥ ያህል ፥ ርቀውልህ ፥ ፍቅረ ፥ እግዚአብሔር ፥ በሰውነትህ ፥ እንደ ፥ አሳት ፥ ይቃጠላል ። አንድም ፥ መከራት ፥ በሰውነትህ ፥ የጸኑ ፥ ያህል ፥ ፍቅረ ፥ እግዚአብሔር ፥ በልቡናህ ፥ ይቃጠላ ል ።

እ ፥ እትየ ፥ ብእሲሰ ፥ ለሊሁ ፥ ወገረ ፥ ፍትወት ።
ወንድሜ ፥ ሰውስ ፥ የፈቲው ፥ ከተማ ፥ ነው ።

ወበከመ ፥ ሁከተ ፥ ሕገብ ፥ በውስተ ፥ ወገር ፥ ከማሁ ፥ ይከውን ፥ ጎበ ፥ ኵሉ ፥ መካን ፥ ዘሀለወ ፥ ቦቱ ።
በከተማ ፥ ሽብር ፥ እንዳለ ፥ ሰው ፥ ከለበት ፥ ሁሉ ፥ ሽ ብር ፥ እንዳለ ፥ የፈቲው ፥ ከተማ ፥ ነው ። አንድም ፥ ከከተማ ፥ ሁከት ፥ እንዳይርቅ ፥ መነኩሴ ፥ ከለበት ፥ በ ታ ፥ ሁከት ፥ አይርቅም ።

ዛቲ ፥ ይእቲ ፥ ወገር ፥ እንተ ፥ ብህለ ፥ ዳዊት ፥ በእንቲኣሃ ።
ሀመሃ ፥ መሥራሕ ፥ መጎጠአት ፥ ማእከላ ፥ ወኢይር ሕቅ ፥ እመርሕባ ፥ ጕህሉት ፥ ብሎ ፥ ዳዊት ፥ የተናገራ ት ፤ ሀገር ፤ ከተማ ፥ ይህች ፥ ናት ። (መዝ ፶፭)

ወድኂነሰ ፥ እምኔሃ ፥ ለእመ ፥ ተጸመነ ፥ ብእሲ ፥ ወጕየ ፥ ነበ ፥ ገዳም ፥ ይድኅን ፥ እምሕማም ።
ከዚህ ፥ የሚድኑበት ፥ ምንድነው ፥ ትለኝ ፥ እንደ ፥ ሆ ነ ፤ ረድኤተ ፥ እግዚአብሔርን ፥ ኀግ ፥ ቢያደርግ ፥ ከ ሰው ፥ ተለይቶ ፤ በበአት ፥ ተክቶ ፥ ቢኖር ፥ ከኀጢአ ት ፥ ይድናል ።

በከመ ፥ ይድኅኑ ፥ እምሁከተ ፥ ወገር ።
ከከተማ ፥ ቢለዩ ፥ ከሽብር ፥ እንዲድኑ ።

አሜሃ ፥ ይረክብ ፥ ሞገስ ።
ወደ ፥ ገዳም ፥ በሐደ ፥ ጊዜ ፥ ፍቅርን ፥ ያገኛል ።

ወይብል ፥ ሠኖ ፥ ተበፋየ ፥ አኮኑ ፥ እግዚአብሔር ።
አለኝታዬ ፥ ማነው ፤ እግዚአብሔር ፥ አይደለምን ፥ ይ ላል ።

ወሶበ ፥ ይፈኢ ፥ እግዚአብሔር ፥ ከመ ፥ ተናዝዝ ፥ እምኵሉ ፥ ያስምዖ ፥ ቃለ ፥ ዘምሉእ ፥ ፍሥሓ ።
እግዚአብሔርም ፥ ከሁሉ ፥ እንደ ፥ ተለየ ፥ በየው ፥ ጊ ዜ ፥ ደስ ፥ የሚያሰኝ ፥ ቃል ፥ ያስማዋል ።

ወያጠብየ ፥ እንዘ ፥ ይብል ፥ ጽናዕ ፥ ውኂደል ።
በርታ ፤ ድል ፥ ንሣ ፥ እያለ ፥ በመከራ ፥ ያጸናዋል ።

እስመ ፥ ኢየኀድገከ ፥ ወኢይገድፈከ ፥ እምእደየ ።
በረድኤት ፥ አልለይኽም ፤ ከኔ ፥ አንደኑት ፥ አለይኽ ምና ።

ውኅበ ፥ ዘሖርክ ፥ መካን ፥ እሄሱ ፥ ምስሌክ ።
ባለኽበት ፥ ቦታ ፥ ከንተ ፥ ጋራ ፥ እኖራለኑ ።

ወለማያ ፥ ዘንተ ፥ ገዝኩ ፥ ዘይኅብር ፥ ውስተ ፥ ጸማ ፥ ይኬልሕ ፥ ከመ ፥ ሕፃን ፥ ዘሰምዐ ፥ ድምፀ ፥ አዉሁ ።
በመከራ ፥ የሚኖር ፤ ጽማዊ ፥ ቢል ፤ በብችንት ፥ የሚ ኖር ፥ መነኩሴው ፥ ይህን ፥ በሰማ ፥ ጊዜ ፥ ያባቱን ፥ ድምፅ ፥ የሰማ ፥ ሕፃን ፥ ደስ ፥ እንዲለው ፥ ደስ ፥ ይለ ዋል ።

ወይብል ፥ ኦ ፥ አባ ፥ ወአቡየ ።
አባቱ ፥ አባቱ ፥ ይለዋል ።

ዘንተ ፥ ብሕቱ ፥ ይረክብ ፥ በገዳ ።
በዚህ ፥ ይህን ፥ ብቻ ፥ ያገኛል ።

ወእምዝ ፥ ይጸንዕ ፥ ልቡ ፥ በተደሞ ፥ ሁከታት ፥ ዘእምኀበ ፥ ጸጋ ፥ እን ተ ፥ ትትዘወክ ፥ ውስቴቱ ፥ ዘእንበለ ፥ ተፈልጦ ።
ከዚህ ፥ በኋላ ፥ ያለ ፥ መለየት ፥ በምትሰጠው ፥ በእግ ዚአብሔር ፥ ቸርነት ፥ የሚገለጹ ፥ ሀብታት ፥ ምሥጢ ራትን ፥ በማድነቅ ፥ ልቡ ፥ ይጸናል ።

መፈድፋደስ ፥ እብል ፥ በእንተ ፥ ሁከታተ ፥ ኅለም ፥ ሐዲስ ፥ ተዐውቶ ፥ ወለብዎ ፥ ዘቀዳማዊ ፥ ዘኢይትከወለን ፥ ይእዜ ፥ ክሚቶታ ።
ይልቁንም ፥ ፈጽሞ ፥ ልንናገራት ፥ የማይቻለን ፥ የሐ ዲስ ፥ ዓለም ፥ ምሥጢር ፥ ቀዳማዊ ፥ ጌታን ፥ ማወቅ ፥ መረዳት ፥ ነው ፥ ብዬ ፥ እናገራለኑ ። አንድም ፥ ታሜ ውቆ ፥ ወታሌብዎ ፥ ገልጸን ፥ ልንናገራት ፥ የማይቻለ ን ፥ ቀዳማዊ ፥ ጌታ ፥ የሚያወርሰት ፥ የመንግሥተ ፥ ሰማያትን ፥ ምሥጢር ፥ ታሰወቀዋለች ፤ ታስረዳዋለ ች ፥ ብዬ ፥ እናገራለኑ ።

ወይኄሊ ፥ በልቡ ፥ ከመ ፥ ኢኮነ ፥ ውእቱ ፥ እምገሃነም ፥ ዓለም ።
ከዚህ ፥ ዓለም ፥ ያልተገኘ ፥ ይመስለዋል ።

ወኢ ፥ እምልደት ፥ ሥጋዊት ።
በሥጋዊ ፥ ልደት ፥ ያልተወለደ ፥ ይመስለዋል ።

ወኢ ፡ ዘተወርሀ ፡ ሰብኣዊት ።
በልና ፡ ምሽት ፡ ወደው ፤ ተሰማምተው ፡ በሚሠራ ት ፡ ግብር ፡ ያልተገኘ ፡ ይመስለዋል ።

እስመ ፡ ፍቅር ፡ ወላዲት ፡ ሞስ ፡ እርስዐቶ ፡ ሞስ ።
ሁሉን ፡ የምታስገኝ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ እንዲዘነጋ ፡ አድርጋዋለችና ።

ወወለጠት ፡ ሁከታቲሁ ።
ልወቅ ፡ ልወቅ ፡ ማለቱን ፡ ለውጣለታለችና ።

ወወሀበቶ ፡ ፍቅረ ፡ ምስለ ፡ ፍቁራኒሁ ፡ ዘኢይትነገር ፡ ባቲ ።
የማይመረመር ፡ ፍቅርን ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፤ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሰዋታዋለችና ።

ዘውእቱ ፡ አርኣያ ፡ መላእክት ፡ ኀጹሓን ፤ ወተወርዞመ ።
ይኸውም ፡ መላእክትን ፡ መምሰል ፤ መላእክትን ፡ ወዳጅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

አሀ ፡ ሚ ፡ መድምም ፡ ወዕፁብ ፡ ይእቲ ፡ ፍቅር ፡ እንተ ፡ ታርእዮ ኪያሃ ፤ ወትቀስፍ ፡ ቦቱ ፡ እንዘ ፡ ኢየእምር ።
እሷን ፡ የምትገልጽለት ፤ ሳያውቅ ፡ በሱ ፡ የምታሳድርበት ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለች ፡ ድንቅ ፡ ረቂቅ ፡ ናት ። አ ፤ ወዮ ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ።

ውዕየ ፡ ብርዐ ፡ ቀለም ፡ እምላህበ ፡ ፍቅርክ ፡ አ ፤ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፤ ከፍቅርህ ፡ እሳት ነት ፡ የተነሣ ፡ የቀለሙ ፡ ብርዕ ፡ ተቃጠለ ።

የማንየ ፡ ደክመ ፡ እምን ፡ ጽሑፍ ።
ቀኝ ፡ እጇም ፡ ጽሮ ፡ ጽሮ ፤ ከመጻፍ ፡ ደከመ ።

አዕይንትየኒ ፡ ተጸስላ ፡ እምጸዳለ ፡ ሥጋክ ።
ከፈትህ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ዓይኖቼ ፡ ፈዘዙ ።

ምድርኒ ፡ ሰስሰት ፡ እምቅድሜየ ።
ምድርም ፡ በፊቱ ፡ ዘረችብኝ ።

ወኮሎ ፡ ግብር ፡ ዘሳዕሌሃ ።
በምድርም ፡ ያለው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ዘረብኝ ።

ልብየኒ ፡ ተደመ ፡ እምእንዘርትክ ።
ልቤም ፡ እንተን ፡ በማንከር ፡ ፈዘዘ ።

ወአነ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ዘኢየእምር ።
እኔም ፡ እንደማያውቅ ፡ ሰው ፡ ሆንኩ ።

ነደ ፡ አዕፅምትየ ፡ እምን ፡ ላህብ ።
ከፍቅርህ ፡ እሳትነት ፡ የተነሣ ፡ ሕዋሳቶቼ ፡ ተቃጠሉ ።

ወተከሥቱ ፡ እንቅዕት ፡ ለስቅዮተ ፡ ሥጋየ ፡ ከመ ፡ ኢየዐይ ።
ክብር ፡ አጥቼ ፡ እንዳልናደድ ፡ ሰውነቴን ፡ ለማክበር ፡ ሀብታት ፡ ምሥጢራት ፡ ተሰጡ ።

አህ ፡ ለውእቱ ፡ ምብኣሕ ፡ ኀጹሕ ፡ ዘውስቴቱ ፡ የሐበርቶን ፡ ገባሪ ፡ ለልሕኮታቲሁ ።
አጣ ፡ ጻድቃንን ፡ ለሚያጸራበት ፤ ለሚያከብርበት ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ።

አህ ፡ ለዝንቱ ፡ ዐጽፈ ፡ ብርሃን ፡ ዘአስሰለ ፡ እምኔነ ፡ ልበሰ ፡ ፍትወት ፡ ዘውስጥ ።
የጎልዮ ፡ ጎጢአትን ፡ ከኖ ፡ ላራቀ ፡ ለወልድ ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ።

ይእዜኒ ፡ እግዚኦ ፡ አብሐኒ ፡ ከመ ፡ አህብ ፡ ቅድሳተ ፡ ለደቂቅከ ።
አውንም ፡ አቤቱ ፡ ለምእመናን ፡ ድርሳንን ፤ መልእክትን ፡ እጽፍ ፡ ዘንድ ፤ ሀብታት ፡ ምሥጢራትን ፡ እገልጽ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘኝ ።

ወአኮ ፡ ዘእውብ ፡ ባሕርየ ፡ ኀጹሐ ፡ ዘአምሕፅንከ ።
ከባሕርይኽ ፡ የሚገኘውን ፡ ምሥጢር ፡ ወስኜ ፡ የምጽፍ ፡ አይደለም ።

ባሕርይ ፡ ዘኢይረክብዎ ፡ ከሰባት ፡ ሰፍቁራኒከ ፡ አዕርጎ ።
ለ ፡ የቀረው ፡ ነው ፤ ያልበቁ ፡ ሰዎች ፡ የማያውቁትን ፡ ምሥጢር ፡ ለወዳጆችህ ፡ ግለጸው ።

ከመ ፡ ኢይኪድዎ ፡ አሕርው ፡ በእንፈሆሙ ፤ እስመ ፡ አነ ፡ ኬድክዎ ፡ ከመ ፡ ሐራውያ ።
እኔ ፡ ሳልበቃ ፡ ጽፌዋለሁና ፤ እሱ ፡ ጽሮታል ፡ ብለው ፡ እንዳይነቅፉት ።

ስብሐት ፡ ለክ ፡ በክመ ፡ አንተ ፡ መድምም ፡ ወመድምማት ፡ ይእቲ ፡ መንክራቲክ ።
አንተ ፡ ድንቅ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ ምሥጢራትህም ፡ ድንቅ ፡ ናቸውና ፤ ምስጋና ፡ ይገባኻል ።

ብውንን ፡ እሙንቱ ፡ ፍቁራኒክ ፡ እስ ፡ በጸዳለ ፡ ሥንክ ፡ ይበርሁ ፡ በሞሱ ፡ ጊዜ ።
ሁል ፡ ጊዜ ፡ በአካልህ ፡ ብርሃን ፡ የሚያበሩ ፡ ወዳጆችህ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወአንተኒ ፡ ትሁየሙ ፡ ርእየ ፡ ሥንክ ።
አንተም ፡ መልክህን ፡ ማየት ፡ ትገልጽላቸዋለህ ።

ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትንግሌ ፡ ምውታን ፡ ቀዳሚት ፡ ለእለ ፡ በክርስቶስ ፡ በክመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ። (ተሰ፬ ፡ ፲፮) ።
ጳውሎስ ፤ መቅድመ ፡ ትንሥኤ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ በክርስቶስ ፡ ላመኑ ፡ መገሥመሪያ ፡ የምትሰጥ ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ ይህች ፡ ናት ።

ብፁዓን ፡ አንትሙ ፡ እ ፡ መንኩሳት ።
መነኰሳት ፤ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናችሁ ።

እስመ ፡ ኮንከሙ ፡ አሐደ ፡ በተሳትፎ ፡ ምስለ ፡ ዋሕድ ፡ ወልደ ፡ እግ ዚአብሔር ።

በመዋሐድ ፡ ከወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁናችኋልና ።

ወበእንተዝ ፡ ምሥጢራተ ፡ አብ ፡ ትትወሀብ ፡ ለክሙ ።

ከወልድ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተዋሐዳችኁ ፡ የአብ ፡ ምሥጢ ር ፡ ትገለጽላችኋለች ።

ወትብሉ ፡ ዘእንበለ ፡ ጎፍረት ፡ ጎሕንስ ፡ ልቡ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብን ።

ያለ ፡ ማፈር ፡ የክርስቶስ ፡ ሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ ስ ፡ አድሮብናል ፡ ትላላችኁ ።

ወይሠርቅ ፡ በውስተ ፡ አልባቢሃ ።

በልቡናችን ፡ ይገለጻል ፡ ትላላችኁ ።

ወኮነ ፡ ብሩሃን ፡ በስብሐቲሁ ።

በሱ ፡ ብርሃን ፡ ብሩሃን ፡ ሁነናል ፡ ትላላችኁ ።

አሌ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ በፈቃድየ ፡ አህጉልዝሙ ፡ ለእሱ ።

እሊሀን ፡ ሀብታት ፡ ምሥጢራት ፡ ወድጇ ፡ በፈቃዱ ፡ አጥቻቸዋለሁና ።

ወርስትየኒ ፡ ክኅነ ፡ ብሔረ ፡ ጽልመት ፡ ዘተደለወት ፡ በዝየ ።

መኖሪያዬም ፡ በጎጢአቴ ፡ የተዘጋጀች ፡ ገሃነም ፡ ሁና ለችና ፤ ወዮ-ልኝ ።

ኦ ፡ አምላኪየ ፡ አእትት ፡ እምላዕሌየ ፡ ልብሰ ፡ ሕማም ፡ ዘገሃነመ ፡ ጽ ልመት ።

ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፤ ወደ ፡ ገሃነም ፡ የሚያወርድ ፡ ኀጢ አትን ፡ ከኔ ፡ አርቅልኝ ።

ወአልብሰኒ ፡ ልብስ ፡ ብርሃን ፡ ቅዱስ ።

የብርሃን ፡ ልብስ ፡ አልብሰኝ ።

ዘውእቱ ፡ አክለ ፡ ሐዲስ ፡ ዓለም ፡ ቅድመ ፡ ፀአትየ ፡ እምዝንቱ ፡ ሥ ጋ ።

ይኸውም ፡ የዓለም ፡ ሐዲስ ፡ የክርስቶስ ፡ አክል ፡ ነ ው ፤ ከዚህ ፡ ከሥጋ ፡ ሳልለይ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ አ ዋሕደኝ ።

ሀበኒ ፡ እግዚኦ ፡ ሥን ፡ ጎጸፊከ ፡ ለበሊዕ ።

ምግብ ፡ ሊሆነኝ ፤ ደስ ፡ ሊያሰኘኝ ፡ ያማረ ፡ መልክህ ን ፡ ሳለጥልኝ ።

ወርእየ ፡ ምሥጢፊቲከ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ጎብኦተ ፡ ውስተ ፡ ሕፅንከ ፡ ለዕትይ ፡ ዘያስተፈሥሕ ።

ልቡናን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መጠጥ ፡ ሊሆነኝ ፡ በባሕ ርይ ፡ ተሠውራ ፡ ያለች ፡ ምሥጢርህን ፡ ሳለጽልኝ ።

ረስየኒ ፡ እግዚኦ ፡ አሐደ ፡ እምአባላቲከ ፡ ውስተ ፡ ሥጋከ ።

አቤቱ ፤ ከሕዋሳትህ ፡ እንዳንዱ ፡ አድርገኝ ፤ ማለት ፤ እንደ ፡ አጅህ ፤ እንደ ፡ እግርህ ፡ አድርገኝ ።

ከመ ፡ እኩን ፡ ድልወ ፡ ለዕትየ ፡ ጽዋህ ፡ ፍሥሓ ፡

እንተን ፡ ለመዋሐድ ፡ እንድበቃ ፡ አድርገኝ ።

ወእአምር ፡ ምሥጢራተ ፡ ተዋሕዶትከ ፡ ምስሌየ ፡ በእምጣን ፡ ይትከሀ ሎን ፡ ለጠባይዓትየ ፡ ድኩማት ።

ከኔ ፡ ጋራ ፡ የተዋሐድኸበትን ፡ ምሥጢር ፡ ላላዋቂ ፡ በሕርዬ ፡ እንደሚቻለው ፡ መጠን ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ።

ተዐቀብኬ ፡ ኦ ፡ እጉየ ፡ ወጸሐቅ ።

ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ በተዐቅቦ ፡ ኑር ።

ከመ ፡ ትኅሥሥ ፡ ፍቅረ ፡ እምላክከ ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ።

የፈጣሪን ፡ ፍቅር ፡ ታገኝ ፡ ዘንድ ፡ በመዓልትም ፡ በ ሌሊትም ፡ ትጋ ።

ወባቲ ፡ ይጠፍኦ ፡ አፍቅሮተ ፡ ነሶ ፡ ሕማም ፡ እምሳዕለ ፡ ነፍስከ ።

በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅረ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋልኻ ል ።

ወለሊሃ ፡ ይእቲ ፡ ዘታውዕዮ ፡ ለጸላኢ ።

የሰይጣን ፡ ማኅል ፡ ዓይኑን ፡ የምትደፈግመው ፡ እ ሷ ፡ ናት ።

ወታስተጋብእ ፡ ሀብታተ ፡ እምን ፡ ማኅደሩ ፡ ለአብ ።

አብ ፡ በሚያድርበት ፡ በልቡና ፡ ሀብታትን ፡ ታሰድራ ለች ።

እም ፡ ይእቲ ፡ ወላዲተ ፡ ሐዲስ ፡ ምሥጢር ፡ እንተ ፡ ሐዲስ ፡ ኀለም ።

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የክርስቶስን ፡ ምሥጢር ፡ የ ምታስገኝ ፡ እናት ፡ ናት ።

ዘውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ያሠርቅ ፡ መንፈሶ ፡ በውስቴትከ ።

ይኸዉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በልቡናህ ፡ የሚያሰድ ርህ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

ወነፍስከኒ ፡ ትትፈሣሕ ፡ ቦቱ ።

ሰውነትህ ፡ በሱ ፡ ደስ ፡ ይላታል ።

ወትከውኖ ፡ ማኅደረ ፡ ምስለ ፡ እቡሁ ፡ ወምስለ ፡ መንፈሱ ፡ ቅዱስ ።

ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ለወልድ ፡ ማደሪ ያ ፡ ትሆነዋለህ ።

እምውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ይፌስየከ ፡ ትግበር ፡ ፈቃደ ፡ ለክርስቶስ ፡ በኃይ ል ።

ከደረብህ ፡ በኋላ ፡ የክርስቶስን ፡ ፈቃድ ፡ ደስ ፡ ብሎ ህ ፤ በርትተህ ፡ እንድትፈጽም ፡ ያደርግኻል ።

ኦ ፡ አኀው ፡ ሰናእትት ፡ ፍትወታተ ፡ ኅለም ፡ እሙስተ ፡ ነፍስን ።

ወንድሞቼ ፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ መውደድን ፡ ከልቡናች ን ፡ እናርቅ ።

ወበእግዚአብሔር ፡ ባሕቲቱ ፡ ንትአመር ።

ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ እንዋሐድ ።

ዘሎቱ ፡ በብሐት ፡ እምአፈ ፡ ሠሎሙ ፡ ፍቁራኒሁ ።

በወዳጆቹ ፡ ቃል ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ።

ወለነኒ ፡ ያስተፍሥሐነ ፡ በእፍትኖቱ ።

እኛንም ፡ በፍቅሩ ፡ ደስ ፡ ያሰኘን ።

አሜን ።

ይሁንልን ፤ ይደረግልን ።

መልእክተ ፡ ኃምሲት ።

ለዝኩ ፡ ዘይሰምዕ ፡ ወዘይትኤዘዝ ፡ ቅዱስ ፡ ሰላም ፡ ለይኅድር ፡ ላዕሌሁ ።

አምስተኛዪቱ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ናት ። ምክሬን ፡ ሰምቶ ፡ በሚታዘዝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከቡር ፡ ሰላም ፤ ጸጋ ፡ ይደርበት ።

እ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ በግዕ ፡ ታስ ፡ ፍቁርከ ።

የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ አንተ ፡ ሰው ፤ የወዳጅህ ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ስማ ። አንድም ፡ የወዳጅህ ፡ የኔን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

እ ፡ እጉየ ፡ ፍቁርየ ፡ ኢንፅልም ፡ ለክርስቶስ ፡ በእንተ ፡ ፍትወትን ፤ አላ ፡ ንትአዘዝ ፡ ሎቱ ።

ወዳጄ ፡ ወንድሜ ፤ ክርስቶስን ፡ አንካደው ። አንድም ፡ አንታዘዝለህም ፡ አንበለው ፤ አንታዘዝለት ፡ እንጂ ።

ለእመ ፡ ፈቀድከ ፡ ትርስዮ ፡ ለክርስቶስ ፡ በውሳጤከ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፡ አፍቅር ፡ ፍቁራኒሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ።

በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ አድርብህ ፡ ክርስቶስን ፡ ልታየው ፡ ብትወድ ፡ ወዳጆቹን ፡ ጸድቃንን ፤ መላእክትን ፤ ዐሥራ ፡ ቃላትን ፤ ቀሰውስትን ፤ መምህራንን ፤ ንስሓን ፡ ሰትጠራጠር ፡ እሊህን ፡ ውደድ ።

ለእመ ፡ ፈቀድኩ ፡ ይልህብ ፡ ዝንቱ ፡ ወትረ ፡ በውስተ ፡ ነፍስከ ፡ አውፅእ ፡ እምኔከ ፡ ፍቅረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ።

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሰውነትህ ፡ ሊ ያድርብህ ፡ ብትወድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ፍቅር ፡ ከል ብህ ፡ አውጥተህ ፡ ጣል ።

እመ ፡ ታፈቅርኑ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ ኢኮንት ፡ ሀገረክ ፡ ከመ ፡ ትኅድር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ በከመ ፡ ወ የእክ ፡ እምክርሥ ።

ሀገርህ ፡ ያይደለች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ከወደ ድህ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ከናት ሀ ፡ ማሕፀን ፡ እንደ ፡ ወጣህ ፡ ዙረህ ፡ ሳታይ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተለይ ።

ወእንተ ፡ ትፈእኮ ፡ ለውእቱ ፡ ጸድት ።

ጸድቅ ፡ ጌታን ፡ ታየዋለህ ።

ኢይትከህልኬ ፡ ከመ ፡ ይኅድር ፡ ክርስቶስ ፡ ኀቡረ ፡ ምስለ ፡ ዓለም ።

ፍቅረ ፡ ክርስቶስና ፡ ፍቅረ ፡ ዓለም ፡ በንድ ፡ ልቡና ፡ ሊኖር ፡ አይቻልም ።

አስተበፅዎከ ፡ ከመ ፡ ትሰምዖ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እንስ ፡ ኢኮንኩ ፡ እምዓለም ፤ ወበእንተዝ ፡ ይጸድኦኒ ፡ ዓለም ፡ እግኅደርየ ፤ ወኢይትክህ ለኒ ፡ ንቢር ፡ ምስሌሁ ፡ እስመ ፡ ይጸልፀኒ ።

እኔ ፡ ከዓለሙ ፡ ወገን ፡ አይደለሁም ፤ ስለዚህ ፡ ከማደ ሪያዬ ፡ ከልቡና ፡ አስወጥቶ ፡ ይሰደኛል ፤ ይጠላኛል ና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ መኖር ፡ አይቻለኝም ፡ ያለውን ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ እግልድኻለኁ ።

ወትረ ፡ የኀድር ፡ ክርስቶስ ፡ ኀበ ፡ ንፍስ ።

ክርስቶስ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በንፍስ ፡ ያድራል ።

ወይሔውጻ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ፅርቅተ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይኅድር ፡ ውስቴታ ።

ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተለይታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያድርባት ፡ ዘንድ ፡ ይጉበኛታል ።

እመ ፡ ትፈቱ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ ጸናሰ ፡ ሥጉ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ፅቡ ፡ ትእዛዘ ፡ ለክርስቶስ ፡ በውስተ ፡ ልቡክ ።

የሦስቱን ፡ አክል ፡ ብርሃን ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ብትወድ ፡ በልቡናህ ፡ የክርስቶስን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ።

ይቤ ፡ ካዕበ ፡ ለሊሁ ፤ ዘያፈቅረኒ ፡ ይዕቀብ ፡ ቃልየ ፤ ወያፈቅር ፡ አቡየ ፤ ወንመጽእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወንገብር ፡ ምዕራፈ ።

እሱም ፡ ባለ ፡ ቤቱ ፡ እኔን ፡ የሚወደኝ ፡ ሕጌን ፡ ይጠብቅ ፤ አባቴም ፡ ይወደዋል ፤ ወደርሱ ፡ መጥተን ፡ ማረፊያ ፡ መሰፈሪያ ፡ እናደርገዋለን ፡ ብሏል ።

ወኀሊ ፡ ይቤ ፡ ወእንተ ፡ ፍቁራኒሁ ፤ ከመ ፡ ኢኮኑ ፡ እምዓለም ፤ ወዘ እንተዝ ፡ ይጸልፆሙ ፡ ዓለም ።

ዳግመኛ ፡ ወዳጆቹ ፡ ሐዋርያት ፡ ከዓለሙ ፡ ወገን ፡ እንዳይደሉ ፤ ዓለሙም ፡ እንዲጠላቸው ፡ ተናገረ ።

ተናጸሜተ ፡ ሠሉ ፡ ትእዛዘ ፡ ፍጥተ ፡ መስቀል ፡ ይእቲ ።

የትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ ነው ።

ዘውእቱ ፡ መንኖ ፡ ፍትወት ፡ ዘዝንቱ ፡ ዓለም ።

ይኸውም ፡ ፍቅረ ፡ ዓለምን ፡ መተው ፡ ነው ።

ወይፈቱ ፡ ፈሊጸ ፡ እምኔሃ ።

ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መለየትን ፡ መውደድ ፡ ነው ።

በከመ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ።

ጳውሎስ ፡ እፈቱሰ ፡ እትፈለጥ ፡ እምዓለም ፡ ብሎ ፡ እ

ንደ ፡ ተናገረ ፤ ይፈቱ ።

በምንስ ፤ ወበተስፋ ፡ እንተ ፡ ብየ ፡ ኀበ ፡ እምሳኪያ ፡ እብል ፡ ጥዩቀ ፡ ከመ ፡ ጎሊና ፡ ዕበ ፡ ይትናዘዝ ፤ ወይከውን ፡ ፅሩቀ ፡ እምትከዘ ፡ ዓለም ፡ ይለብሶ ፡ ለክርስቶስ ።

በባለ ፡ ሚልነት ፤ በተስፋ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ባገኘሁት ፡ ዕውቀት ፡ ጎሊና ፡ በተዘክሮ ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ ከማሰብ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስን ፡ እንዲዋ ሐደው ፡ አስረድቼ ፡ እናገራለኁ ።

ወእመ ፡ ይትወተት ፡ እምኔሁ ፡ ጎልሮ ፡ ምግባሬት ፡ ይረክዐ ።

ዓለማዊ ፡ ግብርን ፡ ማሰብ ፡ ከሱ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ጌታን ፡ ይዋሐደዋል ።

ወነፍስኒ ፡ ዕበ ፡ ትገድፍ ፡ እምኔሃ ፡ ተዛውዖ ፡ ዘዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ይዜ ምር ፡ በውስቴታ ፡ መንፈስ ፡ ኀቡኣተ ፡ ምሥጢራቲሁ ፡ እንተ ፡ ኢት ትነገር ።

ነፍስም ፡ ሥጋዊ ፡ ጨወትን ፡ በተወች ፡ ጊዜ ፡ የማት መረመር ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢርን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በ ሷ ፡ አድሮ ፡ ይናገራል ።

ወለወኢ ፡ በዝየ ፡ ኀቡኣተ ፡ ምሥጢር ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የምናገረው ፡ ምሥጢር ፡ አለኝ ። አንድም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ አለ ።

ወፅውዕ ፡ ውእቱ ፤ ወኢይትዐወቅ ።

ያውም ፡ ምሥጢሩ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፤ አይታወቅም ።

ወሳእቱ ፡ ለጸድቃንሰ ፡ ታስተርኢ ፡ ጽድቅ ።

ምሥጢር ፡ ለጸድቃን ፡ ትታወቃለች ፡ እንጂ ።

እንሰሐስሑ ፡ ኀበ ፡ ውሒዝ ፡ ዘውእዝ ፡ ለእስትዮትክሙ ።

እናንተን ፡ ለማክበር ፡ ወደ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ በ እግረ ፡ ጎሊና ፡ ሒዱ ።

አይኑ ፡ ዝንቱ ፡ ዘንዋልመ ፡ ሀየንተ ፡ ዝንቱ ።

ይህን ፡ ዓለም ፡ በዚያ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ፈን ታ ፡ ያን ፡ ዓለም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምንለውጥበት ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ምንድር ፡ ነው ። አንድም ፡ የወዲያዉ ን ፡ ዓለም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንለውጠው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ምንድር ፡ ነው ። (ሐተታ) ፤ ውሽ ፡ በ ቀበሮ ፡ ለውጠኝ ፡ ቢሉው ፡ የሚያደምጠዉን ፡ ትቼ ፡ የሚያለምጠዉን ፡ እንዳለ ። አንድም ፡ ይህን ፡ ዓለ ም ፡ በክርስቶስ ፡ ለውጠን ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሔደን ፡ ነበር ። ዳግመኛ ፡ ክርስቶስን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንለ ውጠው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ወይ ፡ ሊተ ፤ አሌ ፡ ሊተ ።

ወዮልኝ ፤ ወዮልኝ ።

ወካዕበ ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ ምዝዕቢተ ።

ዳግመኛ ፡ ዕጽፍ ፡ ወዮታ ፡ አለብኝ ።

አ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘፈደይክ ፡ ዕዳን ፡ ዘረከብኩ ፡ እመንገለ ፡ ፍትወት ፡ እከ ት ፡ በደምክ ፡ ንጹሕ ።

በክፉ ፡ ፈቃድ ፡ የመጣብን ፡ እዳችንን ፡ ይምሀን ፡ አ ፍሰሀ ፡ የከፈልህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ።

ክሥት ፡ አዕይንተ ፡ አልባቢኦ ፡ ከመ ፡ ናእምር ፡ ኀበ ፡ አይ ፡ መካን ፡ ንሑር ።

የምንሔድበትን ፡ በታ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዓይነ ፡ ል ቡናችንን ፡ ግለጽልን ።

ወብርሃንኪኒ ፡ ዘያበርህ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ ለአስተፍሥሖተ ፡ ቅዱሳኒክ ፡ ውእቱ ፡ ይምርሐኒ ፡ ኀቤክ ።

ወዳጆችህን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ የሚያ በራ ፡ ብርሃንህ ፡ መርቶ ፡ ወዳንተ ፡ ያድርሰኝ ።

ወመንፈስከ ፡ እግዚኦ ፡ ያቁመኒ ፡ ማእከለ፡ሙ ።

በመላእክት ፡ መከከል ፡ እንድቆም ፡ ያድርገኝ ።

በዝየኒ ።

በዚህ ፡ ዓለም ።

ወበኀለመ ፡ ብርሃንከ ።

በወዲያዉም ፡ ዓለም ። አንድም ፤ በዝየኒ ፤ በነጽሮ ። ወበዓለመ ፡ ብርሃንከ ፤ በተዋሕዶ ።

ወመወረኒ ፡ መጽሐፎ፡ሙ ፡ ከመ ፡ አስብክ ።

መጽሐፍ ፡ ካልኑ ፡ ብሎ ፡ አስብክ ፡ ብሏል ፡ እንጂ ፤ ቅዳሴሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ምስጋናቸውን ፡ እንዳመሰ ግን ፡ አድርገኝ ።

ወእሰብሕክ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በስብሐት ፡ ዘኢይሰግዕ ።

በእዝነ ፡ ሥጋ ፡ የማይሰማ ፡ ምስጋና ፡ ከርሰቸው ፡ ጋ ራ ፡ እንዳመሰግን ፡ አድርገኝ ።

ረስየኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍጥረተ ፡ ሐዲስ ፡ እንተ ፡ ትመስል ፡ እርኢያ ፡ ሥን ክ ፡ እስክ ፡ እረስዕ ፡ ዘትካት ፡ ጠባይዕየ ።

አቤቱ ፤ የቀደመ ፡ ባሕርዬን ፡ እስክዘነጋ ፡ ድረስ ፡ አ ንተን ፡ የምመስል ፡ ሐዲስ ፡ ፍጥረት ፡ አድርገኝ ።

ስብሐት ፡ ስውሐዘ ፡ ፍቅርክ ፡ እንተ ፡ ኢትትነገር ።

ለማትመረመር ፡ ለብዙ ፡ ፍቅርህ ፤ ዓለምን ፡ ላዳንህባ ት ፡ ፍቅርህ ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ።

ርኅው ፡ ደዲክ ።

ደጅህ ፡ የተከፈተ ፡ ነው ።

ወአልዖ ፡ ዘይበውእ ።

የሚገባ ፡ የለም ፡ እንጂ ።

ክሙት ፡ ስብሐቲክ ።

ምስጋናህ ፡ የተገለጠ ፡ ነው ።

መአልዩ ፡ ዘይኄሊ ።
የሚያስበው ፡ የለም ፡ እንጂ ።

ብርሃንህ ፡ ይሠርት ፡ በቅድመ ፡ አዕይንቲነ ።
ብርሃንህ ፡ በፈታችን ፡ ያበራል ።

መኢንፈቅደ ።
እኛ ፡ አንሸዉም ፡ እንጂ ።

የማንክ ፡ በፍሕት ፡ ለመጥፎ ።
ቀኝ ፡ እጅህ ፡ ለመስጠት ፡ የተዘረጋች ፡ ናት ።

መአልዩ ፡ ዘይሥኢ ።
የሚቀበል ፡ የለም ፡ እንጂ ።

ትስሕበነ ፡ ወትገድፈነ ።
በረድኤት ፡ አቅርበህ ፡ በመከራ ፡ ትጥለናለህ ።

መኢንሰምዕ ።
እኛ ፡ ግን ፡ አንሰማም ።

ታደንግፀነ ፡ በእፍርሆትክ ፡ አንተ ፡ ተቀስሐት ፡ ምስለ ፡ ምሕረትክ ።
ከይቅርታህ ፡ ጋራ ፡ በተቀላቀለች ፡ መከራ ፡ ታስደነ ግጠናለህ ። በጥቃ ፡ መዓቱ ፡ ሀሎ ፡ ምሕረቱ ፡ እንዲ ል ።

መኢንጉይይ ፡ ጎቤከ ።
እኛ ፡ ዳን ፡ ወዳንተ ፡ አንቀርብም ።

እ ፡ አምላክነ ፡ ኄር ፡ ተሠይል ፡ ላዕለ ፡ ሕርትምናን ።
ቸር ፡ ፈጣሪያችን ፡ ሆይ ፤ በጎጢአት ፡ የጐሰቈለ ፡ ሰ ውነታችንን ፡ ይቅር ፡ በል ።

እ ፡ ፈጣሪን ፡ ብዙን ፡ ርኅራኄ ፡ መግህል ፡ ተሠይል ፡ ላዕለ ፡ ድኅምን ።
ቸርነትህ ፡ ርኅራኄህ ፡ የበዛ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ሆይ ፤ ደክ መን ፡ የሠራነዉን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በለን ።

እ ፡ አቡን ፡ ምሉእ ፡ ምሕረት ፡ መአስተሰርዮ ፡ ለሊከ ፡ ለአል ፡ እምን ብ ፡ ርእስከ ።
ምሕረትን ፡ ይቅርታን ፡ የተመላህ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፤ አንተው ፡ ከራስህ ፡ ለምንልን ። (ሐተታ) ፡ ከበላዩ ፡ ሌሳ ፡ ጌታ ፡ የለምና ፤ እምኀበ ፡ ርእስከ ፡ አለ ።

መአክብረነ ፡ መአቅርበነ ፡ ጎቤከ ፤ እስሙ ፡ ኀሕነሰ ፡ ኢንረትድ ፡ አስተብ ተዮተክ ።
አንተን ፡ መለመን ፡ እንወድምና ፤ በግድ ፡ ሥራ ፡ አ ሠርተህ ፡ ወዳንተ ፡ እንድንቀርብ ፡ አድርገን ።

አመዕእ ፡ ነፍሳቲነ ፡ እምግበ ፡ ሙታሌ ፡ ዘለሊነ ፡ ሞታሌ ፡ ርእሰነ ፡ ኀበ ፡ ብርሃንክ ፡ ዘበአማን ።
በረታዳችን ፡ ከታሰርንበት ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ ሰውነታች ንን ፡ አውጣ ፤ ግለት ፤ ወደን ፡ ከታሰርንበት ፡ ከዚ ህ ፡ ዓለም ፡ ፍቅር ፡ ወዳንተ ፡ ፍቅር ፡ ሰውነታችንን ፡ ለይልን ።

ኀሕነሰ ፡ ኢንፈቅድ ፡ መጺአ ።
እኛ ፡ ዳን ፡ ወዳንተ ፡ መምጣትን ፡ አንወድም ።

ኀይልክ ፡ ይግለአ ፡ እግዚኦ ።
አቤቱ ፡ ከሃሊነትህ ፤ ፍቅርህ ፡ ዓለምን ፡ ድል ፡ ይነሣ ልን ።

ወያውዕእነ ፡ እምቀላየ ፡ ተሠተሞ ፡ ዘወረድነ ፡ ውስቴቱ ።
በወረድንበት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍቅር ፡ ሠሞመን ፡ ከ መቅረት ፡ ያውጣን ።

እግዚኦ ፡ አእትት ፡ እምቅድመ ፡ ገጽነ ፡ መንጠላዕተ ፡ ምሥዋር ፡ ዘይ ገለብባ ፡ ለዐይን ፡ ጎሊናን ፤ መአልባበ ፡ ነፍስን ፡ እምርአየ ፡ ብርሃንክ ፡ ዘበአማን ።
አንተን ፡ ከማወቅ ፡ ዐይነ ፡ ልቡናችንን ፤ ዐይነ ፡ ነፍሳ ችንን ፡ የሚሸፍነው ፡ የጎልዮ ፡ ጎጢአትን ፡ ከገጸ ፡ ልቡናችን ፡ አርቅልን ።

ወቦቱ ፡ ይኩን ፡ ኑዛዜን ፡ ወትረ ፡ በኢይሰላ ።
አንተን ፡ በማየት ፡ የምናገኘው ፡ ተድላ ፡ ደስታችን ፡ ከንተ ፡ ባለ ፡ መለየት ፡ ይሁን ።

በክሡት ፡ ገጽ ፡ ወንጎበር ፡ ስኅለመ ፡ ኀለም ፤ አሜን ።
ለዘላለሙ ፡ በባለ ፡ ሟልነት ፡ እንድንኖር ፡ ይሁን ።

መልእክተ ፡ ሳድሲት ።

እዝዘሙ ፡ ለእንው ፡ እ ፡ አብ ፡ ከመ ፡ ኢይሥሉ ፡ በስመ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ጸአምላስ ፡ አብላን ፤ በዙሉ ፡ ነገርሙ ፡ ኢይዝክሩ ፡ ስሞ ፡ በመ ሐላ ፡ ግሙራ ።
ስድስተኛዪቱ ፡ መልእክተ ፡ ይሁኝ ፡ ናት ። ከዚህ ም ፡ በሐሰት ፡ እየ ፡ ማሉ ፡ መቅሠፍት ፡ ሲታዘዝባቸ ው ፡ እይቶ ፡ ይሀን ፡ ይጽፍለታል ። የማጎበር ፡ አ ባት ፡ የምትሆን ፡ አንተ ፤ እንደ ፡ ባለ ፡ ነፎች ፤ እን ዳላመኑ ፡ ሰዎች ፡ በነገራቸው ፡ ሁሉ ፡ ስመ ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ጠርተው ፡ እንዳይምሉ ፡ አርድእትን ፡ ምከራቸው ፤ አስተምራቸው ።

መኢይፀሉ ፡ ዘእንፀለ ፡ እመ ፡ መአልዩ ።
እውነቱን ፡ እውነት ፤ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ ይበሉ ፡ እን ጂ ፤ ስሙን ፡ ፈጽሞ ፡ በመሐላ ፡ እንዳይጠሩ ፡ ምከራ ቸው ።

ዝንቱስ ፡ ወፂይ ፡ እክይ ፡ ዘያርኤት ፡ እምእግዚአብሔር ፤ ወይፈስሆን ፡ አብላን ፡ በገጹው ።
ይህ ፡ በሐሰት ፡ መማል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነ

ት ፣ የሚለይ ፤ ሑሩ ፣ እምኔየ ፣ እንድንበል ፣ የሚያደርገን ፣ ጥኑ ፣ ጎጢአት ፣ ነው ።

ርጉም ፣ ውእቱ ፣ ዝሱ ፣ ዘይምሕል ፣ በሐሰት ፣ በስመ ፣ እግዚአብሔር ።

በሐሰት ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ስም ፣ ጠርቶ ፣ የሚምል ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ ርጉም ፣ ነው ። (ዘፀኋ ፣ ፯)

እስመ ፣ ኢኮነ ፣ ዘያፈቅሮ ፣ ለእግዚአብሔር ፤ እላ ፣ ጸላኢሁ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ውእቱ ፣ ዘበአግን ።

የእግዚአብሔር ፣ እውነተኛ ፣ ጠላቱ ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ ወዳጁ ፣ አይደለምና ።

በከመ ፣ ሰሊሁ ፣ ከሠተ ፣ ሊተ ፣ እግዚአብሔር ፤ ወእርስየኒ ።

እሱ ፣ እግዚአብሔር ፣ በራእይ ፣ እንደ ፣ ገለጸልኝ ፤ በ ወንጌልም ፣ እንዳስረዳኝ ።

ወአገበረኒ ፣ ከመ ፣ አጠይቀ ፣ በጽድት ።

ጽፈ ፣ አስረዳህ ፣ ዘንድ ፣ ጻፍ ፣ አለኝ ።

እስመ ፣ በዛቲ ፣ ራእይ ፣ ጠግፀ ፣ ሥጋየ ፣ ዲበ ፣ አፅጽምትየ ፣ እምብዝኀ ፣ ገኃር ።

በዚች ፣ ራእይ ፣ ጊዜ ፣ ከመጨነቅ ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ ሥጋዬ ፣ ከጥንቴ ፣ ጋራ ፣ ተጣማቷልና ።

እስመ ፣ ከመዝ ፣ ወሰነ ፣ ሊተ ፤ ወይቤለኒ ፣ አንሰ ፣ ኢይሁብ ፣ ጸጋየ ፣ ለነፍስ ፣ እንተ ፣ ኢትርፀድ ፣ እምኀ ፣ ስቡሕ ፣ ስምየ ፤ ወኢትንፍር ።

ክቡር ፣ ስሜ ፣ በሐሰት ፣ ሲጠራ ፣ ሰምታ ፣ ለማትፈራ ፤ ለማታፍር ፣ ሰውነት ፣ ጸጋዬን ፣ አልሰጥም ፣ ብሎ ፣ ወስኖ ፣ ነግሮኛልና ።

አላ ፣ ታስተሐትረኒ ፣ በድፍረት ።

ደፍራ ፤ ሳታፍር ፣ ትንቀኛለች ፤ ታቃልለኛለች ፣ እንጂ ።

ወአንተኒ ፣ አ ፣ መፍቀሬ ፣ እግዚአብሔር ፣ ቅናዕ ፣ በእንተ ፣ ስሙ ፣ ቅዱስ ፣ ዕበ ፣ ይጼወል ፣ በአፈ ፣ አብዳን ።

እግዚአብሔርን ፣ የምትወድ ፣ አንተም ፤ ባላዋቆች ፣ አንደበት ፣ ስመ ፣ እግዚአብሔር ፣ ሲጠራ ፣ ሰምተህ ፣ ቅና ።

ወለዝሱ ፣ ዘይንብር ፣ ቅድሜክ ፣ ዘንተ ፣ ገሥጾ ፣ ወአሕዝና ።

በፈትህ ፣ ስመ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ጠርቶ ፣ የሚምለዉን ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ ምከረው ፤ በቀኖና ፣ እዘን ፣ በለው ።

ሕያው ፣ ውእቱ ፣ እግዚአብሔር ፣ ከመ ፣ በዝኩ ፣ ጊዜ ፣ ዕበ ፣ እዜክር ፣ ውእተ ፣ ራእየ ፣ ያንቀሰቅል ፣ ልብየ ፤ ወይደንግፅ ፣ እምኍለ ፣ ቍጥዓ ው ።

ያየሁትን ፣ መቅሠፍት ፣ ባሰብሁት ፣ ጊዜ ፣ ልቡናዬ ፣ እንዲነዋወጥ ፤ ከቍጣው ፣ የተነሣ ፣ እንዲደነግጥ ፣ እግዚአብሔር ፣ ምስክሬ ፣ ነው ።

ብፁዕ ፣ ውእቱ ፣ ዘይለምዕ ፣ ወየዐትብ ።

የኔን ፣ ምክር ፤ ትእዛዝ ፣ ሰምቶ ፣ የሚጠብቅ ፣ ሰው ፣ ንዑድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ብፁዕ ፣ ውእቱ ፣ ዘያፈቅር ፣ ለፍቁር ።

ፍቁር ፣ ጌታን ፣ የሚወድ ፣ ንዑድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

ወዘኢይትዋከፍ ፣ ዘንተ ፣ ንገረ ፣ እምአፈ ፣ አብዳን ።

ይኸን ፣ መሐላዉን ፣ ካላዋቆች ፣ አንደበት ፣ የማይቀበል ፤ ማለት ፤ አምል ፣ ቢሉት ፣ የማያምል ፣ ንዑድ ፣ ክቡር ፣ ነው ።

አንሰ ፣ እምይእዜሰ ፣ አረምም ፣ እምተናግሮ ።

እኔስ ፣ እንግዲህ ፣ ወዴህ ፣ ከመናገር ፣ ዝም ፣ አላለኁ ።

አሐዱ ፣ ሀየንተ ፣ ዝሱ ፣ ኮን ፣ ሊተ ፣ ዝኩ ፣ ዘበእንቲኣሁ ፣ ዝሱ ፤ ወኢይትከሀሉ ፣ ያርምም ።

እሱ ፣ ስላዘዘ ፣ ሁሉ ፣ የሚያመሰግነው ፤ ሁሉን ፣ ከመ ርዳት ፣ ዝም ፣ ማለት ፣ የማይቻለው ፣ ጌታ ፣ ስለ ፣ ሁሉ ፣ ፈንታ ፣ በቃኝ ። እንድም ፣ ሁሉ ፣ እሱን ፣ ለማ መስገን ፣ የተፈጠረ ፤ ሁሉ ፣ እሱን ፣ ከማመስገን ፣ ዝም ፣ ማለት ፣ የማይቻለው ፣ ጌታ ፣ ስለ ፣ ሁሉ ፣ ፈንታ ፣ በቃኝ ፤ ከንየ ፣ እንዲል ።

ለቡ ፣ ኦ ፣ እጉየ ፣ ዘንተ ፣ ምሥጢረ ፣ ዘውእቱ ፣ ሕይወተ ፣ ዓለም ፣ ልዑላዊ ።

ወንድሜ ፣ ሆይ ፤ ይኸን ፣ የወዲያዉን ፣ አነዋወር ፣ ምሥጢር ፣ ዕወቅ ፤ አስተውል ።

እስመ ፣ በዓለም ፣ ዘኢየኀልፍ ፣ ንከውን ፣ ጽጉባን ፣ እምፍቅረ ፣ ሥጉ ።

በማያልፈው ፣ ዓለም ፣ የሚወደድ ፣ መልኩን ፣ በማየት ፣ ደስ ፣ ብሎን ፣ እንኖራለንና ፤ ዕወቅ ፤ አስተውል ።

ዝ ፣ ውእቱ ፣ ፍጻሜ ፣ ዝሱ ፣ ግብር ።

የሥራው ፣ ሁሉ ፣ ፍጻሜ ፣ ነጽሮ ፣ ነው ።

ብፁዓን ፣ እሙንቱ ፣ እለ ፣ ይሰክሩ ፣ በፍቅርከ ፣ ኦ ፣ አምላኪየ ።

ፈጣሪዬ ፣ ሆይ ፤ በፍቅርህ ፣ የሚሰክሩ ፣ ንዑዳን ፣ ክቡራን ፣ ናቸው ።

እስመ ፣ ዕበ ፣ ስክሩ ፣ ይረክቡ ፣ ተዝውዖ ፣ ዘኢያረምም ።

በፍቅርህ ፣ በሰከሩ ፣ ጊዜ ፣ የማያቋርጥ ፣ አንክሮ ፣ ተደሞን ፣ ግንዘብ ፣ ያደርጋሉና ።

ይረስዑ ፣ ዘቀዳሚ ፣ ምግባሮሙ ።

የቀደመ ፣ ሥራቸውን ፤ መከራቸውን ፣ ይዘነጋሉ ።

ወዕዎ ፣ ኦ ፣ እጉየ ፣ ወርኢ ፣ ጣዕሞ ፣ ለእሁን ፣ ኄር ፣ ዘከመ ፣ እፍ ፣ ይተዕም ።

ወንድሜ ፤ ከጣዕም ፣ ደርሰህ ፣ እንደ ፣ ምንም ፣ ደስ ፣ እንዲያሰኝ ፣ ጣዕመ ፣ ጸጋዉን ፣ ዕወቅ ።

መእለፅ ፡ ኢንሥኡ ፡ መከራሃ ፡ አኮ ፡ ዘትትዐወቆሙ ፡ ለንባር ፡ ግሙራ ።

መከራዋን ፤ መከራኑቷን ፤ ጻጋዋን ፤ ጸጋኑቷን ፡ ላላመቱ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢነግሯቸው ፡ የምትረዳቸው ፡ አይደለም ።

ለሊሁ ፡ ወሀበሙ ፡ ጣዕመ ፡ ለፍቁራኒሁ ።

እሱ ፡ ጣዕመ ፡ ፍቅሩን ፡ አሳደረባቸው ።

ወፀቱ ፡ ያስኮርሙ ፤ ወያስተሐውዞሙ ።

በጣዕመ ፡ ፍቅሩ ፡ ያሰከራቸዋል ፤ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ።

ለሊሁ ፡ ይትረግሕ ፡ በሙ ።

በመከራቸው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ወሶሙኒ ፡ ያስተፈሥሖሙ ፡ በነፍሱ ፡ ለሊሁ ፡ ሠናየ ፡ ምን ፡ ዘእክሉ ።

በነፍሱና ፡ በአካሉ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ መልኩ ፡ ያማረ ፡ እሱ ፡ በአካሉ ፡ ተገልጾ ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ።

ወሶሙኒ ፡ ኀበ ፡ እርኣያ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ይዌልጠሙ ።

እነሱንም ፡ በጌትነቱ ፡ እሱን ፡ ወደ ፡ መምሰል ፡ ይለውጣቸዋል ።

ለሊሁ ፡ መርዓሆሙ ፡ በእስተርእዮቱ ።

ታይቶ ፡ የሚዋሐዳቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወበዝብዛኩ ፡ ያስተፈሥሖሙ ።

በመዋሐዱም ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ።

ይኔጽርዎ ፡ በውሰጤሆሙ ፤ ወይትሐሠዩ ።

አድሮባቸው ፡ ያዩታል ፤ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ።

ይሠርቅ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ።

በልባቸው ፡ አድሮ ፡ ይገለጻል ።

ወያነብሩ ፡ ሥኖ ።

መልኩን ፡ አይተው ፡ ያደንቃሉ ።

ብዕዕት ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ለሊሃ ፡ ትከውን ፡ መጽሔተ ፡ አርእላ ።

ሰውነቷ ፡ ጠርቶላት ፡ ራሷን ፡ የምታይ ፡ ነፍስ ፡ ንፅድ ፡ ክብርት ፡ ናት ።

ወባቲ ፡ ትፌእኖ ፡ ለክርስቶስ ፡ በውስቴታ ።

በልቡናዋ ፡ ጽርየት ፡ ክርስቶስን ፡ የምታየው ፡ ንፅድ ፡ ክብርት ፡ ናት ።

ለሊሁ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ ደብር ፡ አልፀ ፡ ዘይፌኢ ፡ ገጽየ ፡ ወየሐዩ ።

እሱ ፡ ፊቴን ፡ አይቶ ፡ የሚድን ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ተናገረ ።

በዛቲስ ፡ ግሑር ፡ ይትረአይ ፤ ወእስክ ፡ ለዓለም ፡ ያሐይሙ ፡ ለእለ ፡ ርእይዎ ።

በልቡና ፡ ጽርየት ፡ ሳን ፡ ይታያል ፤ ያዩትንም ፡ ለዘላለሙ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ያሞራቸዋል ።

ፍሥሓ ፡ ለፍቅርክ ፡ አ ፡ እምላክን ።

ፈጣሪያችን ፡ ሆይ ፤ ለፍቅርህ ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ።

እስመ ፡ አልክቱ ፡ አስ ፡ ፕዕምኖ ፡ ለፍቅርክ ፡ ጸልዕኖ ፡ ለሠላ ፡ ተድላ ።

ከጣዕመ ፡ ፍቅርህ ፡ የደረሱ ፡ ሁሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ ጠልተዋታልና ።

መልእክት ፡ ሳብዒት ።

ተያቀብ ፡ አ ፡ እጉየ ፡ እምእለ ፡ ያግብኦ ፡ ነፍሶሙ ፡ ወነፍሰ ፡ አንሥሆሙ ።

ሰባተኛዪቱ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ናት ። ከዚህም ፡ ተሾም ፡ ብለጠታል ፤ እሱም ፡ አልሾምም ፡ ብሏል ።

አልሾምም ፡ በማለቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድብኝ ፡ ይሆንን ፡ ብሎ ፡ አዝንዋል ፤ ስለዚህ ፡ ይጽፋል ።

ወንድሜ ፡ ሆይ ፤ ተሹመው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከሚጐዱ ፤ የወንድሞቻቸውንም ፡ ሰውነት ፡ ተሾሙ ፡ እያሉ ፡ ከሚጐዱ ፡ ሰዎች ፡ ተጠበቅ ።

እስ ፡ ያስተሐምሙ ፡ በግብር ፡ ጎሳፍያት ።

ጎላፊዉን ፡ ሳብር ፡ ከሚያስቡ ።

ወይኤዝዙ ፡ ዝሙ ፡ መኳንንት ።

እገሌን ፡ ሹመናል ፤ እገሌን ፡ ሽረናል ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ መኳንንት ፡ ከሚያዙ ፡ ሰዎች ፡ ተጠበቅ ።

ናሁ ፡ ወድቁ ፡ እምኀበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአቅሞ ፡ ፍትወቶሙ ፡ ሕርትምት ።

ክፉ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ብለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚወደው ፡ ከትሩፋት ፡ እነሆ ፡ ተለዩ ።

ወይፈትዱ ፡ ዝሙ ፡ ይግበሩ ፡ ሶሙ ፡ አዕርክተ ፡ ብዙኃን ።

ብዙ ፡ ወዳጅ ፡ ሊያበጁ ፡ ይወዳሉ ።

ዝሙ ፡ ይኩንሙ ፡ ሕዝበ ፡ ዘይትኤዘዙ ፡ ለአጋንንት ፡ ሀሞከያን ፡ ህድኣት ።

ተዐቅበን ፡ ለሚያፈርሱ ፡ ለአጋንንት ፡ የሚታዘዙ ፡ ወገኖች ፡ ይሆንዋቸው ፡ ዘንድ ።

ወእመኒ ፡ አገበሩክ ፡ አ ፡ እጉየ ፡ አውሥኦሙ ፡ በትሕትና ፡ ተወኪለክ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ወንድሜ ፤ ግድ ፡ ተሾም ፡ ቢሉህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምነህ ፡ በትሕትና ፡ ሁነህ ፡ መልስላቸው ።

ወበሶሙ ፡ አንስ ፡ ወፃእኩ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዝመ ፡ አድጎኖ ፡ ለነፍስየ ፡ እምዝንቱ ፤ ወለኦ ፡ ለአድጎኖተ ፡ ክልኣን ።

እኔ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በምናኔ ፡ የተለየኁ ፡ ነፍሴን ፡

ከሎኔ ፡ ከገሃነም ፡ አድናት ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ሌሎቹን ፡ ለማዳን ፡ አይደለም ፡ ብለህ ፡ መልስላቸው ።

መግሳበርየ ፡ በኣትየ ፡ ይእቲ ።

ማሳበር ፡ እንጂ ፡ ይሰፋል ፡ ብለን ፡ ነው ፡ ቢሉህ ፤ የኔ ፡ ማሳበሬ ፡ በኣቴ ፡ ነው ፡ በላቸው ።

ወጉባኤየኒ ፡ ዘሊተ ፡ ጎሊናትየ ፡ እሙንቱ ።

ጉባኤ ፡ እንጂ ፡ ይበዛል ፡ ብለን ፡ ነው ፡ ቢሉህ ፤ የኔ ፡ ጉባኤ ፡ ሕዋሳቶቼ ፡ ናቸው ፡ በል ።

ወበሕግም ፡ ዘጎፅሌየ ፡ ወጸሳዕለ ፡ እሉ ፡ ይደልወኒ ፡ እኩን ፡ ሊቀ ።

በሕገጋትና ፡ በጎጣውእ ፡ ላይ ፡ ልሾም ፡ ይገባኛል ። ኖላዊ ፡ በበግዕና ፡ በተሰላ ፡ እንዲሾም ። አንድም ፡ በሕዋሳቴና ፡ በጎጣውእ ፡ ላይ ፡ ልሾም ፡ ይገባኛል ።

እምከመ ፡ መራዕክምሙ ፡ በመናይ ፡ ለስብእ ፡ ሴትየ ፡ ሶጴሃ ፡ ይደልወኒ ፡ አስተሐምም ።

ሕዋሳቴን ፡ በሚገባ ፡ ሠራርቼ ፡ ያኖርኋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሌሎቹም ፡ ልሾም ፡ ይገባኛል ።

እስመ ፡ በእሉ ፡ እግሕፀንኒ ፡ እግዚእ ፡ ዅሉ ፡ ክሙ ፡ እፅቀበሙ ።

ሕዋሳቶቼን ፡ እጠብቃቸው ፡ ዘንድ ፤ እመኒ ፡ ዐይን ከ ፡ ታስሕተከ ፡ ምልኃ ። ወእመኒ ፡ እዴከ ፡ ታስሕተከ ፡ ምትራ ። ወእመኒ ፡ እግርከ ፡ ታስሕተከ ፡ ምትራ ፡ ወግድፋ ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ ሾሞኛልና ።

ወእምኳልአንሰ ፡ አነ ፡ ኢ ፡ እኩን ፡ ንኪረ ።

ሌሎቹን ፡ ከመ ፡ በቅ ፡ ግን ፡ እለይ ፡ ዘንድ ፤ ኢትኩንኩ ፡ ከመ ፡ ኢትትኩነኩ ። እስመ ፡ ዘአፅበየ ፡ ርእሶ ፡ የጎሥር ፤ ወዘአትሐተ ፡ ርእሶ ፡ ይከብር ፡ ብሎ ፡ አዘዘኝ ።

ወእመኒ ፡ ፈበዝንቱ ፡ ተምዑ ፡ ኅፅሌክ ፡ እልክቱ ፡ እሉ ፡ ይስሕቡክ ፡ ጎበ ፡ ሚመት ፡ ኢትደንግፅ ።

ተሾም ፡ የሚሉህ ፡ እሊህ ፡ ቢቆጡብህ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማፍረስ ፡ ይሆንብኛል ፡ ብለህ ፤ ይጣሉኛል ፡ ብለህ ፡ አትደንግጥ ።

እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ፈቃዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈድፋደ ።

የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ከመሾም ፡ ይልቅ ፡ አለ ፡ መሾም ፡ ነውና ።

ቀናኢሰ ፡ ኢይፈእሮ ፡ ለብርሃን ።

ለሹመት ፡ የሚቀና ፡ ሰው ፡ ጌታን ፡ አያየዉም ።

እስመ ፡ ይሔምዮሙ ፡ በቅንአቱ ፡ ለብሩሃን ።

በቅተው ፡ የተሾሙትን ፡ በቅናቱ ፡ እገሌ ፡ ለዚህ ፡ ሹመት ፡ ይበቃልን ፡ እያለ ፡ ይነቅፋቸዋልና ።

ዘወትረ ፡ ያንጉረጕር ፡ ብእሲ ፡ ያምፅየ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሹመኝ ፡ እያለ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚበጸበጽ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያሳዝነዋል ።

ዘያሴፅል ፡ ርእሶ ፡ እስክ ፡ ሊኦል ፡ ይወርድ ።

ለሹመት ፡ እበቃለኁ ፡ የሚል ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ይወርዳል ።

ወዘያቴሕት ፡ ርእሶ ፡ ተመሰለ ፡ ክመ ፡ አምላኩ ።

ለሹመት ፡ አልበቃም ፡ የሚል ፡ ሳን ፡ ፈጣሪዉን ፡ ይመስላል ። አሱን ፤ ወተግሕሠ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ እንዲለው ።

ዘያፈቅር ፡ እስተሐምሞ ፡ ይትጌበር ፡ ለዕይጣን ፡ ዝሙት ።

ለሹመት ፡ ማስተንተን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ዝሙት ፡ ለሚያሠራ ፡ ሰይጣን ፡ ይታዘዛል ።

ወዘያፈቅር ፡ ሕዝባውያን ፡ በተሳትፎ ፤ ጸላኢሁ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

በሹመት ፡ አንድ ፡ በመሆን ፡ ባለ ፡ ነጮችን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቱ ፡ ነው ።

ወዘያፈቅር ፡ ቅዱሳን ፡ ፍቁሮሙ ፡ ውእቱ ፡ ለመላእክት ።

ጻድቃንን ፡ የሚወድን ፡ መላእክት ፡ ይወዱታል ።

አጽንዕ ፡ ነፍስከ ፡ እ ፡ ሀነይ ፡ ዘከማየ ።

እንደኔ ፡ ያለህ ፡ አንተ ፡ ሰነፍ ፤ አልሾምም ፡ በማለት ፡ ሰውነትህን ፡ አጽና ።

ናው ፡ እምድኅረ ፡ ንስቲት ፡ ይመጽኡ ፡ ምሴት ፤ ወትንውም ፡ አዕፈዝ ፡ እምጻማ ፡ ኅለም ፤ ወእምዝ ፡ በጊዜ ፡ ጽባሕ ፡ ትትነሣእ ፡ በፍሥሓ ።

እነሆ ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶ ፡ ይመሸል ፤ ከድካምህ ፡ ወርፈኽ ፡ ትተኛለህ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ ብሎህ ፡ ማለዳ ፡ ትነሣለህ ። እንዲህ ፡ ማለት ፤ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሞት ፡ ይመጣል ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድከም ፡ ወርፈኽ ፡ በመቃብር ፡ ትኖራለህ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ ብሎህ ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ትነሣለህ ።

መልእክት ፡ ሳምኢት ።

በከመ ፡ ኢይትክህለን ፡ ንትፉአይ ፡ በበይናቲን ፡ ገጸ ፡ ለገጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ይገሥጉቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘእፍኣ ።

ስንተኛዉቱ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ናት ። በፋና ፤ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እስበሳችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ መተያየት ፡ እንዳይቻለን ።

እግሁኬ ፡ ኢንፊኢ ፡ ጎፁኣተ ፡ ንፍስን ።
እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ የነፍሳችንን ፡ ሕዋሳት ፡ አናደም ።

ወኢይትከህለን ፡ ከመ ፡ ንትፈሣሕ ፡ በምሥጢራት ፡ እለ ፡ ዘሙስቴቶን ፡ ዘእንበለ ፡ በብርሃኑ ፡ ስፈጣሪ ።
የጌታ ፡ ብርሃን ፡ ቢያድርብን ፤ ቢዋሐደን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከልተዋሐደን ፡ ለሕዋሳተ ፡ አፍአ ፡ በተሰጡ ፡ ምሥጢራት ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ አይቻለንም ።

ወበእንተዝ ፡ አንሰ ፡ አነክር ፡ አፍቅሮተከ ፡ እንተ ፡ ኢትትዌለጥ ።
ከዚህም ፡ አትርሳኝ ፡ ብሎ ፡ ልከበታል ። ስለዚህ ፡ ንገር ፡ የማትለወጥ ፡ ፍቅርህን ፡ አደንቃለት ።

እስመ ፡ እንዘ ፡ ኢትፈኢ ፡ ሥርቀተ ፡ ሕይወት ፡ በውስተ ፡ ንፍስየ ፡ ግሙራ ፡ ተወሙከ ፡ ስሥርቀተ ፡ ሕይወት ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ በንፍስከ ፡ ዘእንበለ ፡ አጽርዖ ፡ ሲሐቂፍትየ ።
ለሰውነቴ ፡ ጸጋ ፡ መስጠቱን ፡ ሳታውቅ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በፍቅር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ለመሆን ፡ በሰውነትህ ፡ ያለች ፡ ፍቅርህን ፡ ጸፍልኝ ፡ ብለህ ፡ ታነሣሣታለህና ።

ወትትህወክ ፡ ንፍስየ ፡ ተቶቢሐ ፡ በሰታረ ፡ መንፈስ ፡ ዘይትህወክ ፡ ውስተ ፡ ልብከ ።
በልቡናህ ፡ በሚታሰብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ በሚያደርግ ፡ ፍቅር ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁን ፡ ሰውነቴ ፡ ለጽፈት ፡ ትነሣሣለች ።

ዘያረምሞን ፡ ለዙሎን ፡ ሁከታት ፡ ከመ ፡ ኢይንበራ ፡ ጎዲረ ፡ ምስሉ ።
በልቡና ፡ እንዳያድሩ ፡ ፍትወታት ፡ እኩያትን ፡ የሚያርቃቸው ፡ ብሎ ፡ ሱታፌ ፡ መንፈስ ፡ ላለው ፡ ቀጸለ ።

ወባሕቱ ፡ እግዚእን ፡ ይፅሚክ ፡ ህየንተ ፡ ፍቅርከ ፡ አመ ፡ ያስተርኢ ፡ በውስተ ፡ ንፍስከ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በሰውነትህ ፡ በተገለጸልህ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ የፍቅርህን ፡ ዋጋ ፡ ይስጥህ ።

እስመ ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ፍቅር ፡ ፍጹም ።
ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ እሱ ፡ ነውና ፤ የፍቅርህን ፡ ዋጋ ፡ ይስጥህ ።

መልእክት ፡ ታስዒት ።

ንገሩኒ ፡ በእንተ ፡ ሀልዎትክሙ ።
ዘጠነኛዪቱ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ናት ። ከዚህም ፡ ጸር ፡ ተነሥቶበትሙ ፡ ጸልይልን ፡ ብለው ፡ ልከጠበታል ፤ ለዚህ ፡ ምላሽ ፡ ይጽፋል ። ያነዋወራችሁን ፡ ነገር ፡ ነገሩኝ ።

ወሰባሕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዳኅናክሙ ፡ እንተ ፡ በእግዚአብሔር ።
በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ከመከራው ፡ ከጸሩ ፡ ስለ ፡ ዳናችኁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገንሁት ።

ወሊተሰ ፡ ለጎሠር ፡ ከመዝ ፡ ሀልዎተየ ።
ጸልይልን ፡ ብለዉታልና ፤ ወራዳ ፡ የምሆን ፡ የኔስ ፡ አነዋወር ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

እበልዕ ፡ ወእሰቲ ፤ ወእነውም ፡ በተሀይዮ ።
እበላለኁ ፡ እጠጣለኁ ፤ ትሩፋቱን ፡ ተዘክሮዉን ፡ ቸል ፡ ብዬ ፡ እተኛለኁ ፤ ከምን ፡ ተችሎኝ ።

ዘይገድፍ ፡ ጎሊናሁ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሴፍ ፡ መሮተ ።
እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፤ ይጠብቀኛል ፡ የሚል ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ሞትን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል ። እፈቱሰ ፡ እትፈለጥ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ።

ይቤለኒ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ።
አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ።

ይ ፡ እመ ፡ እንዘ ፡ አሐውር ፡ አነ ፡ በፍናት ።
መንገድ ፡ ስሔድ ።

አው ፡ እንዘ ፡ እቀውም ፡ ጥቃሃ ።
መንገድ ፡ ስገሥም ።

እው ፡ በእፍኣ ፡ እምኔሃ ፡ ዕበ ፡ እእጎዝ ፡ ከመ ፡ እኒል ።
ልሔድ ፡ ብዬ ፡ ሳስብም ፡ ቢሆን ። አንድም ፡ ትሩፋት ፡ ስሠራ ፤ ትሩፋት ፡ ስገሥምም ፡ ቢሆን ፤ ልሥራ ፡ ብዬ ፡ በሰብኑ ፡ ጊዜ ።

ይመጽአኒ ፡ አርምሞ ፡ እምጎበ ፡ ጎይል ፡ አኃዚተ ፡ ሱስ ።
ሁሉን ፡ ከምትገዛ ፤ ሁሉን ፡ ከምትወስን ፡ ከባሕርየ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንክሮ ፡ ተደሞ ፡ ይመጣብኛል ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ።

ወዕቤሃ ፡ እረስዕ ፡ ሀላዊየ ፤ ወዘሱ ፡ ዘለተ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ አነዋወሬን ፤ ሥራዬን ፡ ሁሉ ፡ እዘነጋዋለኁ ።

ወአንክር ፡ ወእደሙ ፡ እምነ ፡ ሥጉ ፡ ስዘመወጢ ።
በተመሥጠ ፡ የወሰደኝ ፡ የጌታን ፡ መልክ ፡ በማየት ፡ ፈጽሞ ፡ አደንቃለኁ ፡ አለኝ ።

ወዘዐ ፡ ልቁ ፡ ለይሰቡ ።
ከአእምሮ ፡ መንፈሳዊ ፡ የደረሰ ፡ ይወቀው ።

ወዘዕ ፡ ኢይክል ፡ ለብዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዐቦ ፡ በዘይክል ፡ ረኪቦ ።
ከአእምሮ ፡ መንፈሳዊ ፡ ደርሶ ፡ ማወቅ ፡ ለማይቻለ

ው ፡ ዓን ፡ እግዚአብሔር ፡ እውቀቱን ፡ ይግለጽለት ።

ወባሕቱ ፡ ኢይትክህለኒ ፡ ከመ ፡ አርኢ ፡ በመሶሎ ፡ ሥልል ፡ እምላቢ ው ፡ ለመኑሌ ፡ ሠሎ ።

ምነው ፡ ጽፈህ ፡ መስለህ ፡ አታሳየኝምን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ የጌታን ፡ መልኩን ፡ በምሳሌ ፡ መስሎ ፡ ማሳየት ፡ አይቻለኝም ።

ወኀሊ ፡ አልዓየ ፡ ጎይል ፡ ከመ ፡ አርኢ ፡ ሥኖ ፡ ስፈጣሪ ፡ በመብጥያ ፡ ቀለግት ።

ጻግመኖ ፡ መልኩን ፡ በቀለም ፡ ጽፎ ፡ ለማሳየት ፡ ከሂ ለ ፡ የለኝም ።

አሌ ፡ ለን ፡ ለእመ ፡ ኮን ፡ ትልእኮትን ፡ ንቴን ፡ እምን ፡ ፍጻሜ ፡ ቅድመ ፡ እግዚእ ፡ ሠሉ ።

ግብልገላችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ፍጹም ፡ ከመሆን ፡ ጥቂት ፡ ከሆነ ።

ምክዕቢት ፡ ወይል ፡ ነውብ ፡ ለንፍሳቲን ፡ እመ ፡ ንበጽሕ ፡ ውስተ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ወፍጻሜ ፤ ወተልእክን ፡ ለእግዚእ ፡ ዴት ።

